ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 222 ሚያዝያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## በረመዳን

## የታየው አብሮነትና መረዳዳት በኢድ አልፈጥር በዓል ሊዳብር ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በረመዷን ወር የታየው አብሮነትና መረዳዳት ይበልጥ በኢድ አልፈጥር በዓል ሊዳብር እንደሚገባ የኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት የፕሬዝዳንቱ አማካሪና የውጭ ግንኙነት ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ገለጹ።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በረመዷን ወር ሰዎች ያላቸውን በማካፈልና በአብሮነት ስሜት እያሳለፉ ይገኛል። ይህ በጎ የመተሳሰብ ልምድ በበዓሉም ወቅት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

የኢድ በዓል የጋራ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶች የሚበለጽጉበትና አንድነት፣አብሮነትና መተሳሰብ የሚጎለብቱበት መሆኑን የገለጹት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፣ ጾሙን በመልካም አስጀምሮ በሰላም ላስጨረሰን ፈጣሪ ምስጋናና የሚቀርብበት ቀን ላይ በዓሉን ከማክበር ባለፈ አቅመ ደካሞችንና ረዳት የሌላቸውን በማገዝ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም እንደገለጹት፤ በበዓሉ ዕለት የዕምነቱ አስተምሮ በሚደነግገው ስርዓት መሰረት የኢድ ሰላት ከመሰገዱ በፊት በየትኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚኖር የቤተሰብ አባል ሁለት ኪሎ ግራም ከግማሽ እህል /ዘካተልፊጥር/ ለአቅመ ደካሞች ይሰጣል።

በዚህም በበዓሉ ዕለት አቅም የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተደስተውና ወገን አለኝ ብለው የሚያስቡበትን መልካም አጋጣሚ መፍጠር ይቻላል

በረመዳን የታየው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## "ሰላም፣ በረከትና ተስፋ በፍቼ ጨምበላላ በዓል ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች ናቸው"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ


**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፡- ሰላም፣ በረከትና ተስፋ በፍቼ ጨምበላላ በዓል ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች መሆናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለሲዳማ ሕዝብ የዘመን መለወጫ ፍቼ ጨምበላላ በዓል

"ሰላም፣ በረከትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## መደበኛ ፓስፖርት ለማግኘት አገልግሎት አሰጣጡ ምቹ ባለመሆኑ ለእንግልት ተዳርገናል

- ተገልጋዮች

## በጉዳዩ ላይ በቅርቡ መግለጫ እሰጣለሁ

- የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- መደበኛ ፓስፖርት ለማውጣት ከፍተኛ መጉላላት እየደረሰባቸው መሆኑን ተገልጋዮች ቅሬታ አቀረቡ። የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ

መደበኛ ፓስፖርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ገበቦ ገብሬ

**ከለውጡ በኋላ የአዲስ አበባን ስምና ክብር የሚመጥኑ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል** ገጽ 4



ዜና



አቶ ተስፋዬ ዘውዴ

# ኢንስቲትዩቱ በ2022 በአፍሪካ ቀዳሚ ተቋም ለመሆን እየሰራ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ ቀዳሚ ተቋም ለመሆን እየሰራ መሆኑ ተገለጸ። 17 ችግር ፈቺ ምርምሮች ተሠርተው ወደ ግምገማ እና ትግበራ ገብተዋል።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ዘውዴ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ በ2022 ዓ.ም ከአፍሪካ ካሉ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩቶች ቀዳሚው ለመሆን እየሰራ ነው።

በዚህም 17 የሚሆኑ ችግር ፈቺ ምርምሮችን እያካሄደ መሆኑንና ከፊሉ ወደ ትግበራ ማስገባታቸውን እንዲሁም የተቀሩትን ምርምሮች ወደ ትግበራ ለማስገባት በግምገማ ላይ መሆናቸውን አብራርተዋል።

ምርምሮቹም በጤና፤ በትምህርት፤ በአገልግሎት አሰጣጥና በፋይናንስ ዘርፍ ግልጋሎት እምርታዊ ለውጥ የሚያመጡ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መተግበሪያዎች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ለአብነት ያህልም በጤናው መስክ፤ የተለያዩ የህክምና ዘርፉን ሊያዘምኑ ወይም ሊያሻሽሉ የሚችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፣ ውስን የሆኑ የህክምና ባለሙያዎች የሚገኙባቸው ሴክተሮች ላይ ተጨባጭ ውጤት ያመጣልም ብለዋል።

የጭንቅላት እጢ፣ የጡት ካንሰር፣ የቆዳ በሽታ ልየታን ማከናወን የሚችሉ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መተግበሪያዎች መዘጋጀታቸውንም አብራርተዋል።

በአዲስ አበባ ስማርት ሲቲ ግንባታ ላይ ወሳኝ ሚና ያላቸው የስማርት ሴኩሪቲ ግንባታዎች እየተካሄዱ እንዳሉ የገለጹት አቶ ተስፋዬ፤ በርካታ ዓለም አቀፍ ሁነቶች በሚካሄዱባት አዲስ አበባም በሺዎች የሚቆጠሩ የአርተፊሻል ኢተለጀንስ ካሜራዎች መገጠማቸውን አንስተዋል። ካሜራዎቹ የፊት ገፅታን እና የመኪና ሰሌዳ ቁጥሮችን የሚለዩ እና የሚመዘግቡ መሆናቸውን አያይዘው ጠቅሰዋል።

በፋይናንስ ሴክተር የውይይት መለዋወጫ ሮቦት (ቻት ቦት) በማዘጋጀት ዘርፉን የሚያዘምኑ ስራዎች እየተከወኑ እንዳሉ በማብራራትም፤ ቻት ቦቶቹ በተመረጡ ሀገርኛ ቋንቋዎች ጭምር ግልጋሎት ይሰጣሉ ብለዋል።

የደረቅ ጭነት የተቀናጀ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መተግበሪያ ደግሞ ለትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሚንስቴር አበርክቶ መተግበሪያዎቹ ግልጋሎት መስጠት መጀመራውን የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ አትተዋል።

በትምህርቱ መስክ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመረጃ አሰጣጥ አገልግሎታቸውን ማዘመን የሚያስችል እና የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችን ማስቀረት የሚያስችል እጅግ ዘመናዊ የሆነ መተግበሪያ ለምቶ ትግበራ ላይ መዋሉንም ጨምረው ጠቅሰዋል።

የተለያዩ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ሥርዓቶች በቅልጥፍና እንዲሰሩ እና ለመረጃ ቋትነት ግልጋሎት የሚሰጥ ማዕከል ግንባታም በተቋሙ ውስጥ ተከናውኗል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የመረጃ ቋት መኖሩ ለተማሪዎችም ይሁን ለመምህራን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቁመዋል።

# "ህብረት፣አንድነትና ፍቅር በፍቼ ጨምበላላ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው"

**አስናቀ ፀጋዬ**

ሐዋሳ፡- ህብረት፣አንድነትና ፍቅር በፍቼ ጨምበላላ በዓል ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው ሲሉ የሲዳማ ክልል ፕሬዚዳንት ደስታ ሌዳሞ ተናገሩ።

ፕሬዚዳንቱ የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ ፍቼ ጨምበላላ በዓልን አስመልክቶ ትናንት በሲዳማ ባህል አዳራሽ በተዘጋጀው መርሃ ግብር ላይ ተገኝተው እንደተናገሩት፤ በፍቼ ጨምበላላ በዓል በሰው ልጆች መካከል ህብረት፣አንድነትና ፍቅር ከፍተኛ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡

በፍቅር፣ በህብረትና በአንድነት የሚከበረው ፍቼ ጨምበላላ፣ የሲዳማ ማህበረሰብ በዚህ መልኩ አንድነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ያስቻለ እና ትልቅ መሰረት ሆኖ ያገለገለ ጠንካራ እሴት መሆኑንም ነው ፕሬዚዳንቱ የገለጹት።

መረዳዳት፣ መደጋገፍና አብሮነት በፍቼ ጨምበላላ በዓል በሰፊው የሚንጸባረቅ መሆኑን የተናገሩት አቶ ደስታ፤ በዚህ በዓል የሌለው ሰው ካላቸው እህት ወንድሞቹ ቤት እንደ ቤቱ ጠግቦ የሚበላበት፣ ያለው ያጣውን የሚያስብበት እንዲሁም ለበዓሉ በቂ ዝግጅት እንዲያደርግ ያለው ለሌለው የሚያካፍልበት የመተሳሰብና የአብሮነት በዓል እንደሆነም አስታውቀዋል።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ፍቼ ጨምበላላ ፍቅርን፣ መረዳዳትንና አብሮነትን እያመጣ ወደፊት መቀጠሉን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ የፍቼ ጨምበላላ ትሩፋት ይህ ብቻ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ ከዚህም በላይ በዓሉ ከአጎራባች ክልል ህዝቦችም ጋር አንድነትና ፍቅር የሚዘራ መሆኑን አመልክተዋል።

እንደ ፕሬዚዳንት ደስታ ገለጻ፤ ፍቼ ጨምበላላ ሕዝቦችን በፍቅር የሚያስተቃቅፍ የፍቅር በዓል ነው፡ ፡ ሌሎች መሰል በዓላትም የዚሁ ገጽታ አላቸው፡፡



የሲዳማ ክልል ፕሬዚዳንት ደስታ ሌዳሞ

ለአብነትም፣ በፍቼ ጫምበላላ ወላይታና ሲዳማ ተቃቅፎ በፍቅር ሲዘምር ማየት የተለመደ ነው፡፡ በተመሳሳይ በጊፋታ ወላይታና ሲዳማ በአንድነት ሲያከብር ይታያል፡፡

የዘንድሮው የፍቼ ጫምበላላ በዓል ዓለም አቀፋዊ ይዘቱን ጠብቆ አንድነትንና አክብሮትን በማጠናከር የሚከበር ሲሆን፤ ሁሉም የበዓሉ ተሳታፊ በዚሁ ስሜት ሊያከብረው ይገባል፡፡ በዛሬው እለትም የፍቼ ጫምበላላ በዓል በጉዱማሌ በአደባባይ በድምቀት ይከበራል።

# የመላው አፍሪካ የንግድ አውደ ርዕይ ለቆዳ ውጤቶች የገበያ ትስስር የሚፈጥር ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የሚካሄደው የመላው አፍሪካ የቆዳ ውጤቶች ንግድ አውደ ርዕይ ለቆዳ ምርቶች የገበያ ትስስር የሚፈጥር መሆኑን የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር ትናንትና በሰጠው መግለጫ እንዳመለከተው፤ 13ኛው የመላው አፍሪካ የቆዳ ውጦቶች የንግድ አውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ከሚያዚያ 12 እስከ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ይካሄዳል። ይህ የንግድ አውደ ርዕይ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበትና የገበያ ትስስር የሚፈጥሩበት ነው።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር ዋና ፀሃፊ አቶ ሰለሞን ጌቱ እንደገለጹት፤ የንግድ አውደ ርዕይ በኮቪድ-19 ተፅዕኖ እና በአለም አቀፉ የገበያ ስርአት መዳከም ምክንያት የተቀዛቀዘውን የቆዳውን ዘርፍ ማነቃቃት የሚያስችል ነው። ይህ በኢትዮጵያ አዘጋጅነት የሚካሄደው 13ተኛው የቆዳ ምርቶች የንግድ አውደ ርዕይም ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር ለማስፋት ትልቅ እድል እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

ማህበሩ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅትና ሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር አውደ ርዕዩን እንደሚያካሂድ አስታውቋል። የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ባለድርሻ አካላትን የሚያገናኝ ትልቅ አህጉራዊ የንግድ ትርኢት ሆኖ ያገለግላልም ብለዋል።

በአውደ ርዕዩም ላይ ከ200 በላይ የቆዳ ፋብሪካዎች፣ የጫማ አምራቾች፣ የቆዳ አልባሳት አምራቾች፣ የማሽነሪዎችና ግብአት አቅራቢዎች፣ የሎጂስቲክስ አቅራቢዎች እና የፋይናንስ ተቋማት ይሳተፋሉ ተብሎ




እንደሚጠበቅ አመልክተዋል።

15 ሺህ የሀገር ውስጥ እና 2 ሺህ የውጭ ሀገር ዜጎች አውደ ርዕይውን ይጎበኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል።

ኢንዱስትሪው በውጭ ምንዛሬ እጥረት፣በግብአት ውስንነት፣ በዘርፉ በቂ የሠለጠነ የሰው ኃይል አለመኖርና በሌሎች ችግሮች እየተፈተነ እንደሚገኘ አውስተው፤ ኢትዮጵያ በዘርፉ የሚገኙ እድሎችን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም ጥራትና ምርታማነት ላይ አተኩራ መስራት እንደሚኖርባት ገልጸዋል።

የተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ተወካይ አቶ ወንዱ ለገሰ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ በትኩረት ከሚሰራባቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ የቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አንዱ ነው። የቆዳ ኢንዱስትሪ በአለም አቀፍ ደረጃ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የገበያ ልውውጥ ያለው የንግድ ዘርፍ ቢሆንም በኢትዮጵያ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ ነው።

አቶ ወንዱ የተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት ለኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎችን ከቴክኖሎጂ ሽግግር እና ገበያ ትስስር ከመፍጠር አኳያ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ይህ አውድ ርዕይ ትልቅ የገበያ ትስስር በመፍጠር ለኢንዱስትሪዎች ትልቅ አቅም የሚያጎለብት መሆኑን አመልክተዋል።

ማህበሩ ከ189 በላይ አባላት ያሉት ሲሆን ሀገሪቱ ያላትን የቆዳ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋልና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ምርታማነትን በመጨመር፤ አሰራርን በማሻሻልና የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን የንግድ ሰንሰለት በማሳጠር ረገድ ትኩረት ተደርገው ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙ ታውቋል።

ዜና

# የኢትዮጵያና የኩባን ግንኙነት ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ እየተሰራ ነው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮ-ኩባን የፓርላሜንታዊ እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለማጠናከር እየተሰራ መሆኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢና አባላት በኢትዮጵያ የኩባ አምባሳደር ጆርጅ ለፌበር ኒኮላስ ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ዶክተር ዲማ ነጎ እንደገለጹት፤ የኢትዮ-ኩባን የፓርላሜንታዊና የቆየ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ማጠናከር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ገንቢ ውይይት ተደርጓል።

የኩባ ሕዝብና መንግስት በወሳኝ ጊዜ ሁሉ ከኢትዮጵያ ጎን በመቆምና ኢትዮጵያውያንን በማስተማር ባለውለታ መሆናቸውን አስታውሰዋል።

ታሪካዊውን የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ግንኙነትም ይበልጥ ለማሳደግ ቋሚ ኮሚቴው የበኩሉን ጥረት ያደርጋል ያሉት ዶክተር ዲማ፣ በዚህ ረገድ ከውጭ ጉዳይና ከሌሎች ተቋማት ጋር በትብብር እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

በኢትዮጵያውያንና በኩባ መካከል በፖለቲካ ፣ በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚና በስፖርታዊ ጉዳዮች የተፈጠሩ ትስስሮችን በማጠናከር የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

በቀጣይም በፓርላሜንታዊና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶችን በሚያጠናከሩ ጉዳዮች ላይ በትኩረት በመስራት የሁለቱን አገራት ታሪካዊ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር ቋሚ ኮሚቴው ጥረት እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ የኩባ አምባሳደር ጆርጅ ለፌበር ኒኮላስ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያና ኩባ የገጠሟቸውን ወቅታዊ ፈተናዎች በመሻገርና አንድነታቸውን በማጠናከር ረገድ በርካታ የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች አሉ። ሀገራቱ የበለጠ ግንኙነታቸው እንዲያድግ የሚረዱ ስራዎችም በቀጣይ ይከናወናሉ ሲሉ ተናግረዋል።

የዛሬ 40 ዓመት በርካታ የኩባ ወታደሮች ለሀገራቸው ሉአላዊነት ሲዋደቁ የነበሩ ኢትዮጵያንን ለመርዳት መምጣታቸውን ያስታወሱት ዶክተር ዲማ፣ አሁን ላይ በሁለቱ ሀገራት መካከል ጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መኖሩን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅትም ከ5ሺህ በላይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በኩባ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉም ብለዋል።

በቀጣይም የሀገራቱን ጠንካራ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግ የሚረዱ ጥረቶች እንደሚከናወኑ ገልጸው፤ በሁለቱ አገራት መካከል ያለውን ፓርላሜንታዊ ግንኙነት ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

የሁለቱን አገራት የሕዝብ ለዝብና ፓርላሜንታዊ ግንኙነት ለማሳደግ የሚረገውን ጥረት የኩባ መንግሥት ይደግፋል ሲሉ አምባሳደሩ አስታውቀዋል።

በቀጣይም በጤና፣ በትምህርት፣ በባህልና በኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን የሁለቱን አገራት ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

ኩባ በኢትዮጵያ ያለውን የቡና ኢንዱስትሪ ለማሳደግና የሁለቱን አገራት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በጋራ የመስራት ፍላጎት አላት ብለዋል።



ፎቶ ዳኜ አበራ

# በስምንት ወራት ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በወባ በሽታ ተይዘዋል

## - ከ16 ሚሊዮን በላይ አጎበር ተሰራጭቷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ ፡- በ2015 በጀት ዓመት በስምንት ወራት ውስጥ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎች በወባ በሽታ መያዛቸው ተረጋግጦ የህክምና አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ የጤና ሚኒስቴር ገለጸ። ከ16 ሚሊዮን በላይ አጎበር ለወረዳዎች መሰራጨቱን አስታውቋል።

የጤና ሚኒስቴር የወባ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ህይወት ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፣ በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ውስጥ 7 ሚሊዮን 629 ሺህ 934 ለሚሆኑ የወባ ህሙማን ተጠርጣሪዎች ቤተ ሙከራ(ላብራቶሪ)እና በፈጣን መመርመሪያ ኪት ምርመራ የተደረገ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 2 ሚሊዮን 116 ሺህ 168 ሰዎች በወባ በሽታ መያዛቸው ተረጋግጦ ህክምና እየተደረገላቸው ነው።

የወባ በሽታ ተጠቂውም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ የጨመረ መሆኑን ጠቁመው፤ከአጠቃላይ በወባ ተጠርጥረው ከተመረመሩት ውስጥ 28 በመቶ የወባ በሽታ እንደተገኘባቸው ገልጸዋል።

ለመጨመሩም እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከልም አየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የዝናብ መቆራረጥ መኖሩ ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የድርቅ መከሰት እና ሌሎች ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች እንደሚገኙበት ተናግረዋል ።

በተጨማሪም ምትክ አጎበር ሊያገኙ ለሚገባቸው 537 ወረዳዎች አጠቃላይ 19 ነጥብ 7 ሚሊዮን አጎበር ተገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ 16 ሚሊዮን 861 ሺህ 580 አጎበር ለወረዳዎች መሰራጨቱን አብራርተዋል።

13 ሚሊዮን 633 ሺህ 639 አጎበር ለተጠቃሚው ማህበረሰብ መሰራጨቱን ዶክተር ህይወት አመልክተው በዚህም ወደ 39 ነጥብ 4 ሚሊዮን ህዝብን ከወባ ትንኝ ንክሻ በመከላከል ከወባ በሽታ መታደግ ተችሏል ብለዋል ።

በሌላ በኩልም አንድ ሚሊዮን 207 ሺህ 897 ቤቶችን በፀረ-ወባ ትንኝ ኬሚካል መርጨት በመቻሉ 5 ነጥብ 5 ሚሊዮን ህዝብን ከወባ በሽታ መከላከል መቻሉን ነው የተናገሩት።

ዶክተር ህይወት በበጀት ዓመቱ 5ሚሊዮን 358 ሺህ 775 ህሙማንን መመርመር የሚያስችል መመርመሪያ ኪት እና አራት ሚሊዮን035 ሺህ 060 ህሙማንን ማከም የሚያስችል ፀረ-ወባ መድኃኒት ተገዝቶ ወደ የጤና ተቋማቱ እየተሰራጨ ይገኛል።



ዶክተር ህይወት ሰለሞን

ተጨማሪ ግዥ በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አማካኝነት እየተካሄደ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ወባ የሕብረተሰብ የጤና ችግር ሲሆን ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በተለይም ሕጻናትን እና ነፍሰ-ጡር እናቶች የበለጠ የሚያጠቃ የጤና ጠንቅ ነው ያሉት ዶክተር ህይወት፤ በሀገሪቱ የወባ ስርጭት ከፍተኛ ከሆነባቸው አካባቢዎች በዋናነት የሰሜን እና ደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍል መሆኑን ጠቅሰዋል።

ወባማ በሆኑ አካባቢዎች ለሚኖረው ሁሉም ህብረተሰብ በየሦስት ዓመቱ የመድህኒትና አጎበር እየተገዛ ለማህበረሰቡ ይሰራጫል፤ ህብረተሰቡም በአግባቡ በመያዝ በትክክል እንዲጠቀምበት ከስርጭቱ በፊት፣ በስርጭቱ ወቅትና ድህረ ስርጭት የተለያዩ የግዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል ነው ያሉት።

ማህበረሰቡ ግቢውንና አካባቢውን ለወባ ትንኝ መራቢያ ምቹ እንዳይሆኑ ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በማፋሰስና በመደልደል እንዲሁም ውሃ ሊያቁሩ የሚችሉ ቁሳቁሶችን (የመኪና ጎማ፣ የሸክላ ስባሪዎች፣ የወዳደቁ ጣሳዎች፣ ወዘተ.) በማስወገድ የወባ አስተላላፊ ትንኝ እንዳትራባ ማድረግ እንደሚጠበቅበት አሳስበዋል።

ህብረተሰቡ የወባ ህመም ምልክቶች ስሜት ካለውም ወዲያውኑ ወደ አቅራቢያው ጤና ተቋም በመሄድ የወባ ምርመራና ህክምና ማድረግ ይኖርበታል ሲሉ ዶክተር ህይወት ተናግረዋል።

# በዞኑ በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር እየተተገበረ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በቤንች ሸኮ ዞን በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር እየተተገበረ መሆኑን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ።

የሌማት ትሩፋት መርሀግብር በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋ ከተደረገ ጊዜ ጀምሮ መንደሮችን በመለየትና የሚሰማሩበትን ዘርፍ በመወሰን ተግባራዊ መደረግ መጀመሩን የቤንች ሸኮ ዞን ግብርና መምሪያ ሀላፊ አቶ መስፍን ጉብላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ በመርሀ ግብሩ 93 ቀበሌዎች ላይ የሚገኙ ከ270 በላይ መንደሮች የወተት መንደር እንዲሆኑ ተመርጠዋል ። ከ33ሺ በላይ አርሶ አደሮችም ከአንድ ሚሊዮን በላይ እንስሳት ዕርባታ ላይ ተሰማርተዋል። ከእነዚህ ውስጥም 700ሺ የሚሆኑት በጎች ሲሆኑ ከ 30 ሺ በላይ የሚሆኑት ደግሞ የተመረጡ የወተት ላሞች ናቸው።

የዶሮ አርባታን በተመለከትም 131 ቀበሌዎች ላይ 281 የሚሆኑ መንደሮች ተመርጠው ከ አንድ ሚሊዮን 400ሺ በላይ ዶሮዎች ማርባት ተችሏል። በዚህ ዘርፍ ላይ ከ15 ሺ በላይ የሚሆኑ አርቢዎች እየተሳተፉ ሲሆን በቀጣይም የተሻለ ምርት ለማቅረብ ዝርያዎችን የመምረጥ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል። በአሁኑ ጊዜም ከ200ሺ በላይ የሚሆኑ የተሻለ ዝርያ ያላቸው ዶሮዎች መለያታቸውን አብራርተዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻም፤ የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር በአካባቢው ላይ የሚታየውን የአቅርቦትና የኑሮ ውድነትን በመቅረፍ ረገድ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ቢሮው ባደረገው ምልከታም በፋሲካ በአል



አቶ መስፍን ጉብላ

በዶሮና በእንቁላል ምርት በፊት ከነበረው የተሻለ የዋጋ ቅናሽ መስተዋሉን ገልጸዋል።

ዞኑ ደኖች የሚገኙበት አካባቢ በመሆኑ በከፍተኛ ሁኔታ ማር የሚመረትበት አካባቢ ነው ያሉት አቶ መስፍን፤ በርካታ አርሶ አደሮች በባህላዊ መንገድ ንብ የሚያንቡ ቢሆንም በሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር ባህላዊ የንብ ቀፎን ውጤታማነቱ በተረጋገጠ በዘመናዊ ቀፎ የመተካት ስራ መሰራቱን አመልክተዋል።

87 የሚሆኑ ቀበሌዎች ላይ 242 መንደሮች ተለይተው 5ሺህ 200 ዘመናዊ ቀፎዎችን በማሰራጨት ንብ ማነብን በዘመናዊ መንገድ ማካሄድ መቻሉንም አንስተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ዞኑ ያሉት በርካታ ወንዞችን በመጠቀም 37 በሚሆኑ ቀበሌዎች ተለይተው 217 በሚሆኑ አርሶ አደሮች 89 የውሃ ኩሬዎችን በማልማት ለአሳ ምርት መዋሉን ተናግረዋል።

የሌማት ትሩፋት መርሀግብር ለበርካታ ወጣቶች ስራ እድል መፍጠር ችሏል ያሉት አቶ መስፍን፤ በተለይም በሚዛን አማን ከተማ 10ሺ የሚሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን በማደራጀት ወደ ስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል ብለዋል።

ዜና


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

# ከለውጡ በኋላ የአዲስ አበባን ስምና ክብር የሚመጥኑ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ከለውጡ በኋላ የአዲስ አበባን ስምና ክብር የሚመጥኑ የልማት ሥራዎች መሰራታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ ተናገሩ። በአራዳ ክፍለ ከተማ ከ342 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ሰው ተኮር የ90 ቀናት ፕሮጀክቶች ተመርቀዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ በትናንትናው ዕለት በተካሄደው የምረቃ ሥነ ስርዓት ላይ እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እና የዓለም ዓቀፍ ተቋማት መቀመጫ እንደመሆኗ መጠን ከለውጡ በኋላ በርካታ የልማት ሥራዎች በከተማዋ ተሰርተዋል። የልማት ሥራዎቹም አዲስ አበባን እንደስሟ አዲስና ውብ እንድትሆን የሚያደረጉ ናቸው።

ከለውጡ በፊት የአዲስ አበባ መንገዶች እና የወንዝ ዳርቻዎች የከተማዋን ስምና ክብር የሚመጥኑ ሥራዎች አልተሰሩም ያሉት አቶ ሞገስ፤ ከለውጡ በኋላ በከተማዋ የተሰሩትና እየተሰሩ ያሉት የልማት ሥራዎች ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጡ ናቸው። በተለይ በ90 ቀናት የሚሰሩ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶች የከተማዋን ውበት እየጨመሩ መጥተዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ሞገስ ገለፃ፤ በ90 ቀናት ፕሮጀክቶች ከሚገነቡት መካከል የህብረተሰቡን ኑሮ የሚያቃልል ዘመናዊ የዳቦ መጋገሪያ፣ የአትክልት መሸጫ ሱቆች፣ የስፖርት ማዕከላት፣ የሕንጻ እድሳት፣ ግቢ ማስዋብ፣ የአረጋውያንና አቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ ታሪካዊ ቅርሶች እድሳት እና ሌሎች በርካታ ሰው ተኮር ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው።

ፕሮጀክቶቹ ለቱሪዝም መስህብነት የሚያለግሉ፣ ወጣቶች ንቁና ብሩህ አዕምሮ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ፣ በዶሮ እርባታና በንብ ማነብ ተግባራት የስራ ዕድል ከመፍጠር ባሻገር ህብረተሰቡ ምግቡን በደጁ የሚያኝበትን ሁኔታ የሚፈጥሩ ናቸው።

የ90 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክት በመንግስት የሥራ ኃላፊዎች፣ በህብረተሰቡ እና በባለሃብቱ ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃትን ፈጥሯል ያሉት ኃላፊው፤ ፕሮጀክቶቹ ሌሎች ሥራዎችን ለመስራት አቅጣጫ የሚጠቁሙ ናቸው። ስለዚህ የአራዳ ክፍለ ከተማ አሁን ያስመረቃቸውን ፕሮጀክቶች የሚያጠናክሩና ሌሎች አዳዲስ ሥራዎችን ይሠራል ብለዋል።

በቤተ መንግስት የተጀመሩት የልማት ስራዎች በከተማዋ በ90 ቀናት ሰው ተኮር የልማት ተግባራት ተጠናክረው መቀጠላቸውን የገለጹት አቶ ሞገስ፤ በከተማዋ በሚከናወኑ የ90 ቀናት ፕሮጀክቶች እና የልማት ሥራዎች ላይ የተሳተፉ አካላትን በከተማ አስተዳደሩ ስም አመስግነዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ሞላ ንጉስ በበኩላቸው፤ ባለፉት ሶስት ወራት በከተማ አመራሩ የቅርብ ድጋፍና ክትትል፣ በባለሀብቶችና በነዋሪዎች ተሳትፎ ከ342 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የነዋሪውን ህይወት የሚቀይሩና የክፍለ ከተማውን ገፅታ የሚያሻሽሉ የልማት ስራዎች ተከናውነዋል ብለዋል።

በሌማት ቱሩፋት እና በከተማ ግብርና ስራዎችም ከስደት ተመላሾችና የክፍለ ከተማው ነዋሪ ተጠቃሚ እንዲሆን አበረታች ጥረቶች መደረጋቸውን ጠቁመዋል።

ከ90 ቀናት የልማት ስራዎች መካከል ክፍለ ከተማውን ውብና ማራኪ የማድረግ ስራ መከናወኑን እና የቤት ችግርን ለማቃለልም ባለስድስትና ባለሶስት ወለል ህንፃዎች በባለሀብቶች እየተገነቡ መሆናቸውንም አስረድተዋል።

በምረቃ ሥነ ስርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል አፈጉባዔ ፋይዛ መሐመድ፣ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሞገስ ባልቻን ጨምሮ የከተማውና የክፍለ ከተማው አመራሮች የተገኙ ሲሆን ፕሮጀክቶቹ በከተማ አስተዳደሩ፣ በክፍለከተማው፣ በባለሃብቱና በሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በጋራ የተገነቡ ናቸው። በዚህም የላቀ አስተዋፅኦ ላደረጉ ተቋማትና ግለሰቦች የእውቅና እና የምስጋና ስጦታ ተበርክቷል።

## “ሰላም፣ በረከትና ተስፋ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በሲዳሚኛ ቋንቋ ባስተላለፉት መልዕክት “እንኳን ለሲዳማ አዲስ ዘመን መለወጫ ፍቼ ጨምባላላ በዓል በሰላም አደረሰን” ብለዋል።

በመልዕክታቸው የዘንድሮውን በዓል የምናከብረው የበዓሉ ምልክት የሆነው የሰላም ችቦ በሀገራችን ውስጥ መብራት በጀመረበት ወቅት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሰላም፣ በረከትና ተስፋ በፍቼ በዓል ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች ናቸው። እነዚህ ምልክቶች ለሕዝባችን ሰላምን አውርደው፣ ድህነትን ቀብረው ወደ በረከትና ብልፅግና ለመጓዝ የዕቅዳችን አካል ናቸው ብለዋል።

ፍቼ ጨምባላላ የሲዳማ ሕዝብ ብቻ ከመሆን አልፎ የዓለም ቅርስ ሆኖ ከተመዘገበ ዓመታትን አስቆጥሯል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

ይህንን ልዩ በዓል በመጠበቅ ለዚህ ትውልድ ላበቁ አባቶቻችን ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል።

የሲዳማ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን እና ወጣቶች፥ የመንግስትን የሰላም፣ የበረከትና የብልፅግና መንገድ ከፍቼ በዓል ጋር ያለውን ዝምድና ጠንቅቆ በማወቅ ሀገሪቱን ከችግር በማላቀቅና የበለፀገች ሀገር ለትውልዱ ለማስተላለፍ በጀመርነው መንገድ ከጎናችን እንድትቆሙ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የሲዳማ ፍቼ ጨምበላላ የአዲስ ዓመት በዓል በዓለም አቀፍ ደረጃ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በቅርስነት ከተመዘገቡት አምስት የሀገራችን ቅርሶች መካከል መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ደግሞ ሰላም የሁሉም መልካም ነገር መሠረት እንደመሆኑ፣ ያለ ሰላም ልማት የማይታሰብ ነው። ሕዝባችን ሰላሙን በማረጋገጥ ፊቱን ወደ ልማት እንዲያዞር የማድረግ የጋራ ኃላፊነት አለብን ብለዋል።

በነቀምት ከተማ ከህዝብ ጋር ውይይት ማድረጋቸውን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ለነበረኝ ቆይታ እና ውይይት ሕዝቡን አመሰግናለሁ ሲሉም መልዕክታቸውን አስፍረዋል።

## መደበኛ ፓስፖርት ለማግኘት አገልግሎት ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በበኩሉ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለቀረበለት ተደጋጋሚ ጥያቄ በጉዳዩ ላይ በቅርቡ መግለጫ እሰጣለሁ ከማለት ውጪ መረጃ ሊሰጥ አልቻለም። በአዲስ አበባ መደበኛ ፓስፖርት ለማውጣትም ሆነ ለማደስ ወደተቋሙ የሚሄዱ ተገልጋዮች በተቋሙ ባለው ምቹ ያልሆነ አሰራር ምክንያት ለከፍተኛ እንግልት እየተዳረጉ መሆኑን ይገልጻሉ። ተገልጋዮቹ እንደሚሉት በተቋሙ አገልግሎቱን ለማግኘት ከሌሊት 9፡00 ጀምሮ ተሰልፎ ወረፋ ከመጠበቅ ጀምሮ ፓስፖርቱ አልቆም ለማግኘት ያለው ሂደት ውስብስብና ለከፍተኛ እንግልት የሚዳርግ ነው።

ነዋሪዎቹ እንደሚሉት ፓስፖርት አገልግሎትን ለማግኘት በኦንላይን አማካኝነት ምዝገባ የሚካሄድ ቢሆንም ከዚያ በኋላ በተቀጠሩበት እለት ሌሊት ወጥቶ ወረፋ መጠበቅ፤ ከዚያም በኋላ ሂደቱን ሲያልፉ ፓስፖርት ለማግኘት ያለው አሰራር ተገልጋይን የሚያማርር ነው።

የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ መዲና ጂብሪል፤ ለልጆቻቸው ፓስፖርት ለማውጣት በስም ዝርዝር ምደባ መሰረት ከካሳንቺስ ፖስታ ቤት እንዲወስዱ የተገለጸላቸው ቢሆንም ከታህሳስ ወር ጀምሮ ከፖስታ ቤቱ አልደረሰም የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

ወደ ኢሚግሬሽን መስሪያ ቤት ተመልሰው መጠየቅ እንዳለባቸው የተነገራቸው ወይዘሮ መዲና፤ ከዋናው መሥሪያ ቤት ወደፖስታ ቤት በየጊዜው እያመላለሷቸው መቸገራቸውን በምሬት አስረድተዋል።

ከዚህ ባለፈ በኢምግሬሽን መግቢያ በሮች ላይ ጥበቃዎችና ተራ አስከባሪዎች ወደ ውስጥ እንዳታስገቡ የሚል ትዕዛዝ ተሰቶናል በሚል ተገልጋዮችን ለመምታት የሚጋበዙ መሆናቸውን ገልጸው፤ በዚህም የሚመለከተውን አካል ለመጠየቅም ሆነ ለማነጋገር እንዳልቻሉ ጠቁመዋል።

ችግሩን በተመለከተ ለማን አቤት ይባላል የሚሉት ወይዘሮ መዲና፤ ዜጎችን የሚያጉላሉ አሰራሮችን ማስተካከልና አገልግሎቱን የተሟላ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

መደበኛ ፓስፖርት ለማውጣት አስፈላጊውን ማስረጃ ከሰጠችና ከተመዘገበች አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን እንደሆናት የምትገልጸው ሌላኛዋ የአዲስ አበባ ነዋሪዋ ወይዘሪት ሰናይት ንጉሴ ነች።

የአስቸኳይ ፓስፖርት ከመከልከሉ በፊት መደበኛ ፓስፖርት ለማውጣት ወደ ዋናው መስሪያ ቤት በመሄድ ማመልከቷን ትገልጻለች።

ኦርጅናል የልደት ካርድ፤ መታወቂያና የትምህርት ማስረጃዎችን እንዲሁም አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ አሟልቻለሁ። አሻራ የሰጠሁ ቢሆንም ማስረጃውን አጣርተን እንጠራሻለን የሚል ምላሽ ቢሰጠኝም እስካሁን ምላሽ አላገኘሁም ትላለች።

እኔ ሻይና ቡና በመሸጥ የምተዳደር ነኝ። በህጋዊ መንገድ ወደ ሌላ አገር ሄጄ ለመስራት ብዬ ፓስፖርት ለማውጣት ፈልጊያለሁ ስትል ሁኔታዋን አስረድታለች።፡

ከለሊቱ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ ተራ ለመያዝ ወደኢምግሬሽን የምትሄድ መሆኑን በመግለጽ፤ እንግልቱ ግን ወደ ኢምግሬሽን በተደጋጋሚ የሄደች ቢሆንም ሳንደውል ለምን ትመጫለሽ የሚል ምላሽ እንደተሰጣትና፤ ጉዳዩን ለተቋሙ ቅሬታ ሰሚዎች ያቀረበች ቢሆንም ምንም ማድረግ እንደማይችሉ እንደተነገራት አስረድታለች።

የጂማ ከተማ ነዋሪው አቶ አብዲሳ ታደሰ በበኩላቸው፤ በከተማው የኢሚግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በተደጋጋሚ ያቀረበው የፓስፖርት ይሰጠኝ ጥያቄ ምላሽ ባለማግኘቱ ወደዋናው መስርያ ቤት ቢመጡም እዚህም ምላሽ ሊያገኝ እንዳተሰጣቸው ይገልጻሉ።

አቶ አብዲሳ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ መረጃዎችን ሁሉ ይዘው መቅረባቸውን በመጥቀስ ከጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎቱን ሳያገኙ እየተጉላሉ መሆኑን ገልጸዋል።

የፓስፖርት ሂደቱን ሲጀምሩ በሶስት ወር እንደሚሰጣቸው የተነገራቸው ቢሆንም በተቀጠሩበት ቀን ፓስፖርቱን መውሰድ እንዳልቻሉ ጠቁመዋል።

የቅርንጫፉን ኃላፊ ስለጉዳዩ ማነጋገሩን የሚገልጸው አቶ አብዲሳ ፖስታ ቤት ሂድ በማለት እንደመለሱለት ቢናገርም ፖስታ ቤት ግን ፓስፖርቱን ሊያገኝ እንዳልቻለ አስረድቷል። በዚህ የተነሳ ወደውጭ አገር ለመሄድ ያሰበውን የቪዛ ዕድል ማጣቱን በምሬት ገልጿል።

ችግሩ ከዋናው መስሪያ ቤት ነው የሚል ምላሽ እንደተሰጠው ጠቁሞ፤ በወቅቱ ወደአዲስ አበባ ኢምግሬሽን ለመምጣት የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጡት በጠየቀበት ወቅት ተጨማሪ 600 ብር በድጋሜ መክፈል እንደሚጠበቅበት የተገለጸለት መሆኑን አስረድቷል፤

የፓስፖርት አገልግሎትለማግኘት እየተጉላሉ የሚገኙ ዜጎች ቀልጣፋ አሰራር እንዲፈጠርና በኢሚግሬሽን አገልግሎትና በፖስታ ቤቶች መካከል ተገቢው መናበብ ሊፈጠር ይገባል ሲሉ ጠይቀዋል።

ጉዳዩን በተመለከተ የኢምግሬሽን፣ ዜግነትና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲን በስልክና በደብዳቤ በተደጋጋሚ በመጠየቅ ምላሽ ለማግኘት የተደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። ኤጀንሲው በጉዳዩ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ እንደሚሰጥ በቃል ደረጃ ቢያሳውቅም ወደሕትመት እስከገባንበት ሰዓት ድረስ ምንም አይነት መግለጫ እንዳልተሰጠ ማረጋገጥ ተችሏል።

## በረመዷን የታየው...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሲሉ አስረድተዋል።

የረመዷን ልዩ መገለጫው የሆነውን በፍቅርና በመተሳሰብ ስሜት የመጠያየቅ ልምድ ማዳበር ይገባል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ ለወገን ደራሽ ወገን ነው በሚል ዕሳቤ የተጎዱትን መደገፍና አብሮነትን ማሳየት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የረመዷን የፆም ወር ትሩፋት የሆነውን የመረዳዳት ባህል የሕዝቦችን አንድነትና ፍቅርን የሚጨምር ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ ከዓመት ዓመት መልካም ተግባራትን እያጠናከሩ በመቀጠል የመረዳዳት ባህሉን ማጎልበት ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል።

በዋናነት በረመዷን ወር የተላበስነውን መልካም አስተሳሰብና ምግባር ከረመዷን በኋላ ባሉት ጊዜያት በማጠናከር ለሀገር ሰላምና ልማት ይበልጥ ማዋል ይገባል ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

እንደ ሀገር የሚያጋጥሙንን የተለያዩ ችግሮችን ሁሉም ዜጋ በጋራ ተረዳድቶ ማለፍ ይገባዋል ሲሉም ረዳት ፕሮፌሰር አደም ተናግረዋል።

ወጣቱ በበኩሉ ሰላሙን በማስጠበቅ በተገኘው የስራ ዘርፍ ተሰማርቶ ችግር የሚፈታበትን መንገድ ማመቻቸትና የሀገሩን ልማት ማስቀጠል ይኖርበታል ብለዋል።

1444 ተኛው የኢድ አልፈጥር በዓል ለሕዝበ ሙስሊሙ የሰላምና የደስታ በዓል እንዲሆን ከወዲሁ መልካም ምኞታቸውን የገለጹት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ ዜጎች ዘር፣ ብሔርና የቆዳ ቀለም ሳይመርጡ ያላቸውን በማካፈል ህብረታቸውን ማጠናከር እንዳለባቸው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሱዳን ሰላም መሆን የኢትዮጵያና የሕዝቦቿ የሁልግዜም ፍላጎት ነው!

ኢትዮጵያና ሱዳን ከጉርብትና ባሻገር በደም የተሳሰሩና የቆየ የጋራ ታሪክ ያላቸው ሕዝቦች ናቸው።ሁለቱ ሕዝቦች ከሚጋሩት ረጅም ድንበር ባሻገር ከጥንት ጀምሮ የባህልና የታሪክ መወራረስ የሚታይባቸውና ዕጣ ፈንታቸውም በአንድ ላይ የተጻፈ ነው።የአንዱ ቤት ሲንኳኳ በቀላሉ ሌላው ቤት የሚሰማውም ለዚህ ነው፡፡

ኢትዮጵያና ሱዳን ከጥንትም ጀምረው ነፃነታቸውን የሚወዱ እና ብሔራዊ ክብራቸውን አስጠብቀው የቆዩ ሕዝቦች ናቸው። ሁለቱ ኩሩ ሕዝቦች ነጻነታቸውን አሳልፈው ላለመስጠት በርካታ መስዋዕትነት የከፈሉና ከየትኛውም ወገን የሚቃጣን ጣልቃ ገብነት የማይቀበሉ ናቸው።የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝቦች በለጋስነት እና በእንግዳ ተቀባይነታቸው ስማቸው ጎልቶ የሚነሳ አገሮች ናቸው።

ሱዳን ከቅኝ ገዢዎቿ ነፃነቷን ከተጎናጸፈችበት እ.ኤ.አ ከ1956 ጀምሮ “በአንጻራዊ ሰላም” የኖረችው ለአስራ አንድ ዓመታት ብቻ ነው።በተረፈ ለ50 ዓመታት ያህል አንዳንዴ የባህል፣ አንዳንዴም የሃይማኖት፣ አልፎ አልፎም የብሔር ጉዳይ የጠብ መነሻ ሆኖ ስትታመስ ኖራለች።የመጀመሪያው የሱዳን የርስ በርስ ጦርነት ከ1955 እስከ 1972 እ.ኤ.አ. ከዚያም ሁለተኛው የሱዳን የርስ በርስ ጦርነት ከ1983 እስከ 2005 እ.ኤ.አ. ተከስቷል። በ1989 እ.ኤ.አ. በሰላማዊ መፈንቅለ መንግሥት አማር ሀሳን አህመድ አል-በሽር ሥልጣን ላይ የወጡ ሲሆን እርሳቸውም በሕዝባዊ አመጽ 2010 ዓ.ም ከስልጣን ወርደዋል።ሆኖም በእነዚህ የችግር ዓመታቶች ሁሉ ኢትዮጵያ ከሱዳን ሕዝብ ጎን በመቆም የምትታወቅ አገር ነች፡፡

የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብንመለከተው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ስልጣን በያዙ ጥቂት ወራት 2010 ዓ.ም አካባቢ ለረጅም ዓመታት ስልጣን ላይ የቆዩት ፕሬዚደንት አልበሽርን ከስልጣን ለማውረድ የተቀሰቀሰው አመጽ የከፋ ጉዳት እንዳያስከትል መልክ በማስያዝና አገሪቱን የሚመሩ የሽግግር መንግስት አባላትን በጋራ ስምምነት እንዲዋቀር በማድረግ ሱዳንን ተጋርጦባት ከነበረው አደጋ መታደግ የቻለችው ኢትዮጵያ ናት፡፡

ሆኖም እአአ 2021 ላይ የሲቪል መንግሥቱ ከስልጣን መወገዱን ተከትሎ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሱዳን በሉዓላዊ ምክር ቤት በሁለት የጦር ጄነራሎች ስትመራ ቆይታለች። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ወጣ ገባ የሚለው የሰላም ድባብ ብዙዎችን ሲያሰጋ ቆይቶ ሰሞኑን ዋና ከተማዋን ካርቱምን ጨምሮ ወደ ጦርነት ተገብቷል።ከሁከትና ብጥብጥ ማትረፍ የሚፈልጉ አካላትም ሱዳንን ወደ ማያባራ ጦርነት እንድትገባ በርካቶች እጃቸውን ለማስገባት ሲሞክሩ ታይተዋል።

አንዳንዶችም ወዳጅ መስለው በመጠጋት የበለጠ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነግስ የራሳቸውን የቤት ስራ በመስራት ላይ መሆናቸውን የሱዳን ብሄራዊ ጣቢያ ጭምር አጋልጧል።ሆኖም የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንዳሉት የሱዳን ሕዝብ ካጋጠመው ሁኔታ ለመውጣት የሚያስችለው ጥበብና ችሎታ ያለው ሕዝብ በመሆኑ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ችግሩን መፍታት ይችላል፡፡

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የምትታወቅበት የገለልተኝነት ፖሊሲ ዛሬም በሱዳን ላይ እንዲተገበር ትፈልጋለች።ኢትዮጵያ የጎረቤት አገራት ችግር ሲገጥማቸው ችግሮቻቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ የምትመክርና ለዚህም በተግባር የምትንቀሳቀስ አገር ነች።የሱዳንም ጉዳይ ከዚህ አንጻር እንዲታይ ትፈልጋለች፡፡

ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን ‹‹የሱዳን ሕዝብ የራሱን ችግር በራሱ እንዲፈታ ለራሱ መተው ያለበት ሲሆን የማንኛውም የውጭጣልቃ ገብነት ዓላማም ሰላምን እና ድርድርን በተመለከተ ብቻ ሊሆን ይገባል። የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ በበኩሉ የሱዳን ሕዝብ የውስጥ ችግሩን በለመደው ጥበባዊ አካሄድ በራሱ እንዲፈታ የሚመኝ እና የሱዳን ሕዝብ ጥቅም ተከብሮ ማየት ትልቁ ፍላጎቱ መሆኑን በድጋሚ እንገልጻለን ›› የሚል መልዕክትም ያስተላለፉት፡፡

ስለሆነም የሱዳን ሕዝብ ችግሮችን በራሱ መፍታት የሚችል ሕዝብ ነውና ለዘመናት ያካበተውን ጥበቡን ተጠቅሞ ችግሩን እንዲፈታ ዕድል ሊሰጠው ይገባል።ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተፈጠረውን ችግር በራሷ መንገድና አቅም የፈታችበት መንገድም ጥሩ ትምህርት ሊሆን የሚችል ነው።የሱዳን ህዝብ በራሱ አቅምና መንገድ ወደ ቀደመ ሰላሙ እና መረጋጋቱ እንዲመለስ በሚያደርገው ጥረት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት የበኩላቸውን አዎንታዊ ድርሻ ለመወጣት ምንግዜም ዝግጁ ናቸው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጠንካራ መከላከያ ሰራዊት፣ ለጠንካራ አገርና ህዝብ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከአገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች አንዱ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራ ይጠቀሳል።መንግስት በጥናት ላይ በተመሰረተ የለውጥ ንቅናቄ አገርን ተራማጅ በሆነ እሳቤ ለማሻገር ከወሰናቸው ውሳኔዎች አንዱ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት እና ለላቀ አገራዊ ተልዕኮ ዝግጁ ማድረግ አንዱ ነው።የአገርና ህዝብን ጥቅም መሰረት በማድረግ የተካሄደው የዚህ መልሶ የማደራጀት ሥራ ጥናት ተጨባጭ እምርታ እንዲያሳይ በየደረጃው ውይይት ተደርጎበት የክልል ልዩ ኃይሎችን ወደ ሌሎች የጸጥታ መዋቅር እንዲታቀፉ የማድረጉ ሥራ ተጀምሯል፡፡

በዚህም ሁሉም ክልል የሚገኙ የክልል ልዩ ኃይሎች ክብርና ጥቅማቸው ተጠብቆ፤ እንዲሁም በራሳቸው ፍላጎት ላይ ተመስርቶ በመከላከያ ሰራዊት፣ በፌደራል ፖሊሲ ወይም በክልል ፖሊስነት እንዲቀላቀሉ እድሉ ተመቻችቶላቸዋል።ይሄንን አልፈልግም ወደ መደበኛ ኑሯችን መመለስ እንሻለን ለሚሉም የመቋቋሚያ ድጋፍ ተደርጎላቸው ፍላጎታቸው የሚጠበቅና የሲቪል ኑሮን የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

የዚህ መልሶ የማደራጀት ተግባር አላማው የአገር ሉዓላዊነት እና የህዝብን ሰላምና ደህንነት ማሥጠበቅ፤ እንዲሁም አገራዊ ልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ መቻል ነው።ከዚህ የዘለለ ግን ምንም አይነት ትርጓሜ ሊሰጠው አይገባም፤ ከዚህ የተለየም ዓላማ የሌለው ነው።በመንግስት በኩል የተሰሙ ተደጋጋሚ መግለጫዎችና ማብራሪያዎችም ይሄን እውነት የሚያጠነክሩ ናቸው።በመሆኑም ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ስራው አገርን መልሶ ከመስራት ጋር ሊታይ የሚገባው ሃቅ ነው፡፡

በዓለማችን ነባራዊ ሁኔታ ጠንካራ የመከላከያ አቅም ያላቸው አገራት ራሳቸውን አስከብረው ሲዘልቁ፤ የመከላከያ ኃይላቸው ደከም ያሉ አገራት ግን ከውስጥም ከውጪም ዘርፈ ብዙ ጫናና ጥቃት ሲደርስባቸው ይስተዋላል።ኢትዮጵያም ምንም እንኳን የመከላከያ አቅሟ ከራሷ አልፎ ለሌሎች ሰላም መስፈን የተረፈ ቢሆንም፤ ይሄንን ክፍታ የበለጠ የማጠናከር ስራ ሊከናወንለት ያስፈልጋል።ለዚህ ደግሞ ከውስጥ ሊሰሩ የሚገባቸውን የቤት ስራዎች መስራት ተገቢ ሲሆን፤ ልዩ ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶችን በመደበኛው አደረጃጀት ውስጥ እንዲታቀፉ መደረጉም የዚህ አንዱ ማሳያ ነው።የዚህ እውን መሆንም ኢትዮጵያ እንደ አገር አንድነትና ሉአላዊነቷ እንዲጠበቅ ከማድረግ ጎን ለጎን የውጪ አገራት ትንኮሳዎችን የምንከላከልበት ጠንካራ አቅም የሚፈጥር ነው፡፡

ምክንያቱም ጠንካራ አገራዊ መከላከያ ኃይሉ የሁሉም ህዝብ አቅም ሆኖ ስራውን እንዲያከናውን፤ ክልሎችም ከዚህ ዝቅ ያለውን ኃላፊነት ወስደው በመደበኛ ፖሊስ የየአካባቢያቸውን ሰላምና ፀጥታ የማስጠበቅ የቤት ስራን እንዲወጡ የሚያደርግ ነው።ይሄን እውነት አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ ከመንግስት በኩል ከተሰጡ መግለጫና ማብራሪያዎች መካከል፤ “ከአሁን በኋላ ክልሎች የፖሊስ ኃይላቸውን አጠናክረው ወንጀልን በመከላከልና አካባቢያዊ ጸጥታን በማስከበር ላይ ይተጋሉ።ከየትኛውም አካል የሚሰነዘር፣ የአገርን ድንበር ህልውናና ሉአላዊነት የሚዳፈር ኃይል ሲነሳ መከላከያ ሰራዊት እርምጃ ይወስዳል” ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የልዩ ኃይልን አደረጃጀት ከአገር ክብር ጋር የተቆራኘ እንደሆነ የገለጹበት ተጠቃሽ ነው፡፡

ከዚህ ባለፈ የመከላከያ ሰራዊት ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ፣ እንዲሁም ምክትል ኢታማዦር ሹም ጀነራል አበባው ታደሰ የሰጧቸው ጥልቅ ማብራሪያዎች እንደሚያስረዱት፤ የክልል ልዩ ኃይሎችን መልሶ የማደራጀት ስራው አንዳንድ የጥፋት አጀንዳ አራማጆች እንደሚሉት ከትጥቅ መፍታትና ከሌላ አሉባልታ ጋር የተያያዘ ሳይሆን፤ የአገርን ህልውናና ሉአላዊነት፣ ክብርና ነጻነት ከማስጠበቅ ጋር የተገናኘ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም የክልል ልዩ ኃይልን መልሶ የማደራጀት ስራ አንዳንዶች እንደሚሉት የበሬ ወለደ ወሬ ሳይሆን፤ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ የአገርን ሰላምና አንድነት፣ ጸጥታና የሰራዊቱን አቋም ከማነጽ ጋር የተያያዘ ተግባር ነው።በሂደቱም ሁሉም የክልል መንግስታት አምነውበት ይሁንታቸውን የሰጡበት፤ ለውጤታማነቱም እየተጉ ያለበት ነው፡፡

የክልል ልዩ ኃይሎችን በዚህ መልኩ መልሶ የማደራጀት ስራው ከዚህኛው ዓላማ ባለፈ፤ ሕገ መንግስትን የማስከበር ርምጃ ነው።ምክንያቱም የክልል ልዩ ኃይልን አደረጃጀት በተመለከተ በህገመንግስቱ የተቀመጠ አንዳችም ድንጋጌ የለም።ይሄ ማለት የክልል ልዩ ኃይል በህገመንግስቱ እውቅና ያልተሰጠው አደረጃጀት ነው ማለት ነው።ስለዚህ ይሄንን ኃይል ወደ መደበኛና ሕጋዊ መዋቅር ማምጣቱ ተገቢም፤ አስፈላጊም ነው፡፡

አሁን እየተሄደበት ያለው መልሶ የማደራጀት ስራ የክልል ልዩ ኃይሎችን ወደህጋዊነት የሚመራቸው አሰራር ነው።ነገሩን በቀና ልብ ማየት ከተቻለ ደግሞ አገራችንን የምናገለግለው በህግ ጥሰት ውስጥ ሆነን ሳይሆን፤ በህግ በተፈቀደ አደረጃጀት ውስጥ ሆነን እንደሆነ የሚያሳየን ርምጃ ነው፡፡

በሌላ በኩል ዛሬ ላይ በመንግስት እየተከናወነ ያለው ተግባር የሕዝብ ጥያቄን የመመለስ ርምጃ ነው።ምክንያቱም የክልል ልዩ ኃይል አደረጃጀት ለምን አስፈለገ? ሲል ለመንግስት ጥያቄ ሲያቀርብ እንደነበር ይታወቃል።በወቅቱ መንግስት ጥያቄውን ተቀብሎ በብዙ ጥናትና ጥልቅ ማሰብ በኋላ ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ ወደትግበራ ተመልሷል።አሁን ላይ የተጀመረው የአደረጃጀት ትግበራ አንድም የህዝብ ጥያቄ ነው፤ አንድም የህገመንግስትን ማስከበር ነው፤ በተመሳሳይ ጠንካራ የመከላከያ አቅምን የመገንባት ጉዞውን የሚያግዝ ነው፡፡

ህገመንግስቱ ለአንድ አገር የሚፈቅደው አንድ መከላከያ ሰራዊትን፤ የፌደራል ፖሊስን እና የክልል መደበኛ ፖሊስን ነው።ይሄ ደግሞ ለፌዴራል መንግስቱም ሆነ ለክልሎች እንደ ደረጃቸው ኃላፊነታቸውን ሊወጡ የሚችሉበትን አቅም ለክቶ የሚሰጥ ነው።ይሁን እንጂ ከዚህ ድንጋጌ ውጪ የተደራጀው የክልል ልዩ ኃይል፤ አገር ችግር ላይ በወደቀች ጊዜ የበኩሉን ሚና የተጫወተ ቢሆንም፤ አደረጃጀቱ ብሄር ተኮር እንደመሆኑ ዘርፈ ብዙ ችግሮች የታዩበትም ነበር።አገራችን በዘር ፖለቲካ፣ በእኔነት ቁርሾ እየተንገዳገደች ባለችበትና አንድነት በናፈቀን ሰሞን የክልል ልዩ ኃይሎች በብሄር ተቧድነው እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ የመባባላቸው ጣጣ የታየውም ለዚሁ ነበር፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ልዩ ኃይልን በተመለከተ በመግለጫቸው ‹የክልሎች ፉክክርና ትብብር በልዩ ኃይል ግንባታ ሳይሆን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ልማትና በዲሞክራሲያዊ ባህል ላይ ሊሆን ይገባል› ያሉትም ለዚሁ ነበር።በዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ህጉን መሰረት ባደረገ መልኩ የመልሶ ማደራጀት ስራው እውን እንዲሆን የግድ ብሏል።ይህ ሲሆን ግን የአደረጃጀት ትግበራው በፍላጎትና በነጻነት ላይ የተመሰረተ፤ ከምንም አይነት ውስጣዊና ውጫዊ ጫና የጸዳ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

ይሄ ማለት ልዩ ኃይሎች እንደፍቃዳቸው ወደፈለጉበት በመግባት (በመከላከያ ሰራዊት አባልነት፣ በፌደራል ፖሊሲና በክልል መደበኛ ፖሊስነት) አገርን ማገልገል ይችላሉ ማለት ነው።ከዚህ ውጪ የሆነ ፍላጎት ያለው የክልል ልዩ ኃይል መብቱ ተጠብቆለት መቋቋሚያ ተሰጥቶት ከማህበረሰቡ ጋር የሚቀላቀልበት ሁኔታ ተመቻችቶለታል።ውሳኔውም አገር የማዳን፣ አገር የማሻገር፣ ህዝብና ትውልድን አንድ የማድረግ መዋቅራዊ ለውጥ ነው።ከዚህ በተጓዳኝ ለሉአላዊነት አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥ ጠንካራ እና ብቁ መከላከያ ሰራዊትን መገንባት ነው።

ለዚህ ደግሞ መከላከያ ሰራዊት በአደረጃጀት፣ በስነልቦና፣ በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ የተገነባ እንዲሆን ያስፈልጋል።ለዚህ የመንግስትን አላማና እቅድ የሚያስፈጽምና የሚተገብር በአንድነቱ የቆመ ህዝብ ያስፈልጋል።ከውስጥም ከውጪም የሚቃጡ ትንኮሳዎችንም በብቃት መመከት የሚቻለው የአገር መከላከያ ሰራዊት እና የክልል ልዩ ኃይል በሚል የተከፋፈለ አቅም ሳይሆን፤ አንድ ጠንካራ የአገር መከላከያ ሰራዊትን እውን ማድረግ ሲቻል መሆኑን በመገንዘብ፤ ሁሉም አካል ለዚህ ዓላማ እውን መሆን የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

## የሱዳን ጉዳይ

የጨረታ Clichy ግን ደግሞ ዛሬም በየአጋጣሚው ጥቅም ላይ እየዋለ ያለ የነጮች ባለ 24 ካራት ወርቅ ይትበሀል አለ። “ጎደኞችህን መርጠህ መጎዳኘት ትችላለህ። ጎረቤትህን ግን መርጠህ ጎረቤት ማድረግ አትችልም።”/ “You can choose your friends, but you can’t choose your family.”/ አዎ አገራችን ከሱዳን፣ ከኤርትራ፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከጅቡቲ፣ ከኬንያና ከሶማሊያ ጋር ጎረቤት የሆነችው መርጧና ፈቅዳ አይደለም። የዛሬ መጣጥፍ ትኩረት በሱዳን ሰሞነኛ አኳኋን ላይ ስለሆነ እዛው ላይ እናተኩራለን።

በሱዳን የተከሰተው ቀውስ በአንድም በሌላ መልኩ ለአገራችን መትረፉ ስለማይቀር ጉዳዩን በቅርበት ሌት ተቀን መከታተል፤ የሁለቱን ወንድማማች ሕዝቦች ዘላቂ ጥቅሞች ከግምት ያስገባ፤ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ታሳቢ ያደረገ፤ የታሪካዊ ጠላቶቻችንን አሰላለፍ በቅጡ የተረዳ፤ ብስለት የተሞላበት፣ በእውቀትና በጥበብ የሚመራ፣ ድንገት በእጅ የገባን አጋጣሚ አሟጦ የሚጠቀምና አሳልፎ የማይሰጥ ዘርፈ ብዙ የሆነ አመራር ይጠይቃል። አጋጣሚን መጠቀም ያለና የሚኖር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መርህ ነው። ይሄን መርህ እንደ ቻይና አሟጦ የተጠቀመበት አገር የለም። ያው አገርን ይሉኝታ አይዛትምና ይሉኝታ እንዳናሲዛት ለማለት ነው።

በሱዳን ጦርና በፈጥኖ ደራሽ ልዩ ኃይል መካከል ባለፈው ቅዳሜ በካርቱም በተቀሰቀሰ ግጭትና ቢያንስ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲገደሉ ከ2000 በላይ ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሱዳን ልዩ ተወካይ አስታውቋል።ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው የኃይል ሚዛኑ ወደ የት እንደሚቀየር ለመናገር በጣም አስቸጋሪ ነው ሲሉ ልዩ ተወካይ ቮልከር ፔርቴስ ተናግረዋል።የሱዳን ፈጥኖ ደራሽ ኃይል ካርቱምን ጨምሮ የአገሪቱን አየር ማረፊያና የግብፅ ጦር የሰፈረበትን ወታደራዊ ቦታዎች መቆጣጠሩን አስታውቋል።

ሁኔታዎች በፍጥነት እየተለዋወጡ ስለሆነ ያን ተቆጣጠረ ይሄን ለቀቀ ብዙ ውሃ የሚያነሳ መረጃ አይደለም። ገዥው ጥያቄ በሱዳን ሰላም፣ ሉዓላዊ የግዛት አንድነትና ህልውና ላይ የደቀነው አደጋ የሚቀለበሰው በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ወይስ በኃይል የሚለው ነው። በጎረቤት አገር ኢትዮጵያ፣ በቀጣናውና በአኅጉሩ ጂኦ-ፖለቲካና ኢኮኖሚ የሚፈጥረው ተጽዕኖ እንዲሁም የግብጽ ሚና እና በሱዳን ቀውስ የአለማቀፉ የተጻጻሪ ኃይላት አሰላለፍ ማለትም ቻይናና ራሽያ በአንድ ወገን አሜሪካ መሩ ምዕራባውያን በሌላ በኩል እንዴት ይሆን የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ።

የአገራችን ትኩረት በበሽታዋ ላይ እንጂ በምልክቱ ሊሆን አይገባም። በውጊያው ግብጽ በቀጥታ ጣልቃ መግባቷ በግልጽ እየተነገረ ነው። ለምን !? ለምንስ ከአል-ቡርሀን ጎን ሆነች !? እነዚህ ጥያቄዎች ከተለያየ ጂኦ-ፖለቲካና ከሕዳሴውና ከቀጣናው አንጻር መተንተንና መብጠርጠር አለባቸው።

በአፍሪካ ጉዳዮች ላይ ጥናት እና ምርምር የሚያደርገው አማኒ አፍሪካ የተሰኘው ተቋም መስራች ዶ/ር ሰለሞን አየለ ደርሶ የሚጠቅሷቸው አንድ የቀጣናው ተመራማሪ ከአራት ዓመት በፊት እንደ ነብይ ሱዳንን፣ ጎረቤቶቻቸውንና ቀጣናውን የሚያሰጋው ሕዝባዊ ተቃውሞው ሳይሆን”በጦሩ ውስጥ የሚፈጠር የእርስ በእርስ ሽኩቻ ነው።”ብለው ነበር። ይሄው ያሉት ደርሷል። ዛሬም ሆነ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሱዳን ፖለቲካ የምንመለከተው ቀውስ ምንጩ ይህ የስልጣን ሽኩቻ ነው። የሁለቱም አጀንዳ የአብዛኛው ሱዳናዊ አጀንዳ አይደለም። ዜጋው ነጻነት፣ ዴሞክራሲ፣ የስራ ዕድል፣ የኑሮ ውድነቱ መረጋጋት፣ ወዘተረፈ እንጂ ጦሩ ስልጣን ላይ እንዲቀመጥ እንደማይፈልግ ባለፉት አራት ዓመታት በነቂስ ወደ አደባባይ በመውጣት ድምጹ አሰምቷል።

በሱዳን ወታደራዊ መሪዎች ከስልጣናቸው በተወገዱበት በጎርጎሮሳዊው አቆጣጠር 1964 እና 1985 ህዝባዊ አመጾች ወቅት “በአገሪቱ ወሳኝ ኃይል የነበረው ጦር ሰራዊቱ እንደነበር የሚያስታውሱት ተመራማሪው ዛሬም እየተስተዋለ ያለው ይሄ ነው ይላሉ። ሱዳንም ሆነ ግብጽ ከዚህ ቀለበት ሰብረው መውጣት አልቻሉም። ቀደም ሲል በዳርፉር ተሰማርቶ የነበረው ጃንጃዊድ የሚባለው የሚሊሺያ ኃይል አሁን “ፈጥኖ ደራሽ የድጋፍ ኃይል” በሚል እንደሚንቀሳቀስ ያስረዳሉ።

ከእነዚህ ኃይሎች ጎን “የማዕከላዊ ተጠባባቂ ፖሊስ” የሚባል ኃይል እና የሱዳን ገዢ ፓርቲ “እስላማዊ ታጣቂ ቡድን” እንዳለም ያብራራሉ። እነዚህ ኃይሎች በሳውዲ አረቢያ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እና ኳታር እንደሚደገፉ የሚገልጹት የፖለቲካ ተንታኙ ሁሉንም እንደ የጻባያቸው አቻችለው መምራት የቻሉት ፕሬዚዳንት አልበሽር ብቻ እንደነበሩ ያሰምሩበታል። ዶ/ር ሰለሞንም በዚህ ትንታኔ ይስማማሉ።

በአልበሽር የመጨረሻ የስልጣን ቀናት በደህንነት ኃይሎች እና በጦር ሰራዊቱ መካከል፤ በተቃዋሚ ሰልፈኞች ላይ እርምጃ በመውሰድ እና አለመውሰድ ላይ አለመግባባት ተፈጥሮ እስከመታኮስ መዳረሳቸው የተነገረ ቢሆንም፤ ከዚያ በኋላ የጎላ ችግር ባለመከሰቱ ስጋቱ የቀነሰ መስሎ ነበር። ስልጣኑን የተረከበው ወታደራዊ ምክር ቤት ከገዢው ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያላቸውን እስላማዊ ሚሊሺያዎች “ተቆጣጥሯል” መባሉም ስጋቱን ትንሽ አርግቦት ነበር። በተለያዩት የጸጥታ ኃይሎች መካከል ለጊዜውም ቢሆን ስምምነት ያለ ቢመስልም በጦር ሰራዊቱ ውስጥ ያለው ልዩነት ግን ጊዜው ጠብቆ ፈንድቷል።

ከአልበሽር ስልጣን መነሳት በኋላ በመሪነት ብቅ ያሉት የሱዳኑ መከላከያ ሚኒስትር ስልጣናቸውን ከአንድ ቀን በኋላ ሳይጠበቅ ያስረከቡ ዕለት መጪው ጊዜ ለሱዳን ክፉ ንግር ነበር። መከላከያ ሚኒስትሩን ሌፍተናንት ጄነራል አዋድ ሞሃመድ ኢብን አውፍን የተኳቸው በተመሳሳይ ወታደራዊ የማዕረግ ደረጃ ያሉት አብደልፈታህ አልቡህራን ናቸው። ሹም ሽሩ ቀጥሎ የብሔራዊ የደህንነት እና የጸጥታ አገልግሎት ኃላፊው ሳላህ አብደላ ጎሽ ስልጣናቸውን ለቅቀዋል። እነዚህ መጠላለፎች የውስጣዊ ችግሩ ብስናት ነበሩ።

የሱዳንን መጻኢ ሁኔታ አቅጣጫ ለማስያዝ ዛሬን ጨምሮ ቀጣዩቹ ቀናት ወሳኝ መሆናቸውን የፖለቲካ ተንታኞች ያሳስባሉ። በአገሪቱ ያለው ፖለቲካዊ ውጥንቅጥ በፍጥነት በሚለዋወጥበት በዚህ ወቅት ከሱዳን ጋር ወደ 1600 ኪሎ ሜትር ገደማ ድንበር የምትዋሰነው ኢትዮጵያ ጉዳዩን የያዘችበትን መንገድ መጠየቅ የአባት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ሰሞኑን የሱዳንን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት ሁለቱ አገራት ልዩነታቸውን በውይይት እንዲፈቱ፤ የውጭ ኃይሎችም በአገሪቱ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት እንዲቆጠቡ አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቷ በኩል ባለፈው ሐሙስ ምሽት ካወጣችው አጭር መግለጫ ውጭ በጉዳዩ ላይ ዝርዝር ማብራሪያ አልሰጠችም። ኢትዮጵያ “በሱዳን እየተካሄደ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ በቅርበት እየተከታተለች” መሆኑን የጠቀሰው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ “ሱዳናውያን አሁን ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ በብቃት እንደሚወጡት ኢትዮጵያኑ ጽኑ እምነት አላት” ብሏል። አገሪቱ “የሱዳናውያን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ የምታከብር” መሆኗንም ጠቁሟል ይለናል የዶቸ ቬለ ዘገባ ።

በቅርብ ጊዜያት በኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ታሪክ ላይና በተለይ በቀጣናው ጉዳይ ተከታታይ ቃለ ምልልሶችን ለሸገር ኤፍ ኤም ሬዲዮ በመስጠት የሚታወቁት ዶ/ር በለጠ በላቸው በበኩላቸው፤ ስለኢትዮጵያና ሱዳን ግንኙነት ሲጠየቁ፣ ‹‹ግንኙነቱ በሦስት መዋቅሮች ይወሰናል፤›› ይላሉ።አንደኛው የሱዳን የፖለቲካ ኃይሎች የኃይል አሠላለፍ ሲሆን ፤ የውጭ ኃይሎች ጫናና የውጭ ግንኙነታቸው አቅጣጫ በሱዳንና ኢትዮጵያ መካከል የቆየውን የግንኙነት ሁኔታ ሲወስን መቆየቱን ያስረዳሉ፡፡

ሱዳን ለበርካታ ጊዜያት መፈንቅለ መንግሥት ሲካሄድባት የዘለቀች፣ ለበርካታ ዓመታት የተረጋጋ መንግሥት ለመመሥረት ስትቸገር የኖረችና የተለያየ የፖለቲካ አሠላለፍ የሚታይባት አገር ናት ይላሉ። ሱዳን ከዚህ በተጨማሪም በራሷ ብቻ መቆም የማትችልና የውጭ ጫና የሚበዛባት አገር ናት።አገሪቱ ከመካከለኛው ምሥራቅ ብዙ ጫና ለማስተናገድ የምትገደድበት ዓረባዊ ማንነት ያላት ናት።የዓረቡ ዓለምና አፍሪካን የምታስተሳስር ናት በሚል ጫናው ከፍተኛ መሆኑንም ዶ/ር በለጠ ያብራራሉ፡፡

በሱዳን ፖለቲካ ውስጥም ቢሆን ብዙ ዓይነት አቋምና የፖለቲካ አሠላለፍ መኖሩን የውጭ ግንኙነት ምሁሩ ያስረዳሉ።የኃይማኖት ርዕዮተ ዓለም በሱዳን ፖለቲካ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለው የሚጠቅሱት ምሁሩ፣ ይህም ሁለት ትልልቅ ጎራዎች መፍጠሩን ይገልጻሉ።አንዱ ጎራ የካትሚያ እስላማዊ የፖለቲካ ሠልፍ ሲሆን፣ በዚህ በኩል እንደ አሺካና ናሽናል ዩኒየኒስት ያሉ ፓርቲዎች ተሰልፈዋል። የዚህ ርዕዮተ ዓለም ጎራ ፖለቲከኞች (ሠልፈኞች) ኢትዮጵያ ጠልና አፍቃሪ ግብፅ ፖለቲካን ማራመድ ባህላቸው መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ከእነዚህ በተቃራኒው የቆሙት ደግሞ የመህዲያ (መህዲስት) ርዕዮተ ዓለም ፖለቲከኞች ናቸው ይላሉ።በዚህ ወገን በተለይ የኡማ ፓርቲ ዋነኛው ሠልፈኛ መሆኑን የሚያስረዱት ዶ/ር በለጠ፣ በዚህ በኩል በአመዛኙ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነትና ጉርብትናን የተሻለ የማድረግ አቅጣጫን የመከተል የፖለቲካ ባህል መኖሩን ያስረዳሉ።የውጭ ግንኙነት ታሪክ አጥኚው እንደሚሉት በሱዳን ሥልጣን ላይ የሚመጡ የፖለቲካ ኃይሎች (ወታደራዊም ሆነ ሲቪል አስተዳደር)፣ በሁለቱ የሃይማኖት ርዕዮተ ዓለሞች ሠልፍ ዥዋዥዌ የመጫወት ልምድ ያላቸው ናቸው።ይህ የጎራ ልዩነት (ሠልፍ) ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ሲጫነው ይታያል፡፡

እንደ መረጃዎቹ”..በአልፋሽቃ መሬቶች የነበሩ (አልቡርሃን-መራሽ) የሱዳን ወታደሮች ከቦታው ለቅቀው እየወጡ ናቸው..” በማለት የተሰራጩ ሲሆን፤ የመረጃው አቅጣጫም ሆነ አመጣጡ ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ መሆኑ ነው የሚያመዝነው..። የአሁኑ የሱዳን ውጊያ ትያትር በዋነኛነት የሃያላን ድርሰት ሲሆን ሁለቱ የጦር መሪዎች በሀያላኑ ስክሪፕት መሰረት የመተወን ሚና ላይ ናቸው ይለናል የዐባይና የቀጣናው አክቲቪስት ሱሌማን አብደላ። ሁለት የኢትዮጵያ ስጋቶች የሚያደርጉት የፍልሚያ ክረት የልቀት resolution ደረጃውን ሲያገኝ ማንን አሸናፊ እንደሚያደርግ ከኢትዮጵያ በኩል ለተመለከተው ለመረዳት ከባድ አይሆንም።

ሁለቱም ተፋላሚዎች የጦር አቅም እንጂ ህጋዊ እውቅናም ሆነ ሕዝባዊ ይሁንታ የሌላቸው ጊዜያዊ ባለስልጣናት እንደመሆናቸው ግጭቱ የቡድን ጥሎ ማለፍ ሽኩቻ የወለደው ነው። ከነሱ አመክንዮ በላይ አንገብጋቢ ጉዳይ ያለባት ካይሮ በበኩሏ አንደኛውን ደግፋ የጦር ጀቶቿን በውጊያው ላይ አሰማርታለች። ግብጽም ኢትዮጵያን ጎትታ በግጭቱ ማሳተፍ ትሻለች።

የሚጠብቃትን ዘርፈ ብዙ ቀውስ በኢትዮጵያ ላይ ማውረድን ትመርጣለች ይለናል ሱሌማን አብደላ። ሰን ዙ የተባለው የቻይና ጄነራልና ስትራቴጂስት”ሁለት ወገኖች ግጭትን ሲመርጡ ከመካከላቸው ቢያንስ አንዱ ተሳስቷል። ምናልባትም ሁለቱም ተሳስተው ይሆናል። “አሸናፊ” የሚሆነውም ቢሆን የተሳሳተ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ግጭት ሁሉንም ስለሚያዳክማቸው ይለናል።

The art of war ላይ “..ድል አድራጊዎች ቀድመው አሸንፈው ወደ ጦርነት ይሄዳሉ፣ ተሸናፊ ተዋጊዎች ግን በመጀመሪያ ወደ ጦርነት ይገቡና ከዚያ በኋላ ነው ለማሸነፍ የሚፍጨረጨሩት..።” የሚለውን እናገኛለን። ኢትዮጵያ ደግሞ ይህን ተጨባጭ አጋጣሚ የምትጠቀምበት አውድ ተፈጥሮላታል። ግብፅን ጨምሮ ሁለቱም የሱዳን ተፋላሚዎች በኢትዮጵያ ጥቅም በኩል ትልቅ ነጥብ የሚጥሉበት ጊዜ ላይ ናቸው።

ለአልፋሽቃ ሉአላዊ እልባት ማግኘት ጉዳይ የኢትዮጵያ የቤት ስራ ሲሆን ከመቸውም ጊዜ በላይ የተመቻቸ አጋጣሚ የተፈጠረበት ወቅት ላይ ነን ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ካይሮ ወደ መዳፋቻን የተጠጋውን የአልፋሻቃ ካርድ የምታመላክተን ከሆነ ጉዳዩ የሱዳኑን ጦርነት ሰፊ ምስል እንዲደበዝዝብንና ቁልፉ ጉዳይ ላይ ከማተኮር እንዳያደናቅፈን ትልቅ ጥንቃቄ ያስፈልገናል የዐባይና የቀጣናው ተሟጋች ወጣት ሱሌማን ያስጠነቅቃል።

አራተኛው ሙሌት ምናልባትም የመጨረሻው የግድቡ ምዕራፍ ሊሆን ይችላልና ጭንቀት ውስጥ የገባችው ካይሮ በሱዳኑ ጦርነት አልቡርሃን በየትኛውም መንገድ ድል ቢቀናው ቢያንስ የተስፋ ስንቅ ይሆናታል። የጀነራሉ ሽንፈት ግን የሞት ሞቷ ይሆናልና ይህን ከመመልከት ሱዳን እንደ ሶሪያና የመን የውክልና ጦርነት አውድማ ብትሆን ትመርጣለችየዚህ ወላፈን ዋነኛ ኢላማዋ ኢትዮጵያ ናትና ወደጫረችው እሳት እንዳታስገባን እያንዳንዷን የካይሮ ቀመር በጥንቃቄ መከታተል ጠቃሚ ጉዳይ ይሆናል። ለዚህ ይረዳን ዘንድ የአገራችንን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በወፍ በረር እንቃኝ።

ኢትዮጵያ በአካባቢው ያላት ተሳትፎና የውጭ ፖሊሲዋ እ.ኤ.አ በ2002 ሥራ ላይ ባዋለችው የውጭ ጉዳይና የብሔራዊ ደኅንነት ፖሊሲና ስትራተጂ ላይ የተመሠረተ ነው።በቅርቡ ያጋጠሟት ውስጣዊ ግጭቶች ቢኖሩም አገሪቱ በአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ቁልፍ ተፅዕኖ ፈጣሪ ናት፣ በክፍለ አኅጉሩ ውስጥ መረጋጋት በመፍጠር በኩልም ወሳኝ ሚና አላት።የኢትዮጵያ መንግሥት በወሳኝ መልኩ ኢጋድና የአፍሪካ ኅብረት በመሳሰሉት ባለብዙ ዘርፍ ኤጀንሲዎች አማካይነት በክፍለ አኅጉሩና በአኅጉሩ ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ ያደርጋል።

በምሥራቅ አፍሪካና በአፍሪካ ቀንድም እንደ አንድ የሚታመን አደራዳሪ ይታያል።ይህ ሚናውም ባለው ተነጻጻሪ ወታደራዊ አቅምና በአካባቢው የሰላም ደኅንነት ዕርምጃዎችና እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚያደርገው ቋሚ ተሳትፎ፣ ሽብርን በመቋቋም ረገድ ያለው አቅምና ተነሳሽነት፣ የአፍሪካዊነት ውርሱና ባለብዙ ዘርፍ መድረኮችን አሟጦ የመጠቀም አቅሙ የመሳሰሉት ባህርያት እንዲዳብሩ አድርጓል።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በወሳኝ መልኩ የሚመሠረተውም ለውስጣዊ ሥጋቶች በሚሰጥ ግብረ መልስ ላይ ነው።ሽብርና የጎረቤት አገሮች ያላቸው የተስፋፊነት ፖሊሲዎች፣ ከኤርትራ ጋር ያለው ግንኙነት፣ በዓባይ ዙርያ ከግብፅ ጋር ያለው የተጠቃሚነት ክርክር የመሳሰሉት ኢትዮጵያ ባላት የሰላምና የማኅበራዊ ዕድገት ጉዞ ላይ የሚያጠሉ የውጭና የውስጥ ሥጋቶች ናቸው።

የውጭ ጉዳይና የብሔራዊ ደኅንነትና ስትራቴጂ ፖሊሲው መሠረታዊ መርሆች ከሁለት አሥርታት በኋላም ቢሆን አግባብነታቸው እየታየ ቢሆንም ኢትዮጵያ ለውስጣዊ ተጋላጭነት ልዩ ትኩረት ከሚሰጠውና ከሚፈለገው በላይ ወደ ውስጣዊ ጉዳዮች ከሚያየው የውጭ ፖሊሲ ይልቅ ሚዛኑ በጠበቀ መልኩ የውጭ ሥጋቶችን ቀድማ ወደምታመክንበትና ሕጋዊ ተጠቃሚነቷንም ወደምታስከብርበት ፖሊሲ መሸጋገር ይጠበቅባታል ሲሉ ዶ/ር መሐሪ ታደለ ማሩ ይመክራሉ፡፡

**ሻሎም !**

**አሜን ።**

# ወቅታዊ

## «የልዩ ኃይል ሪፎርም እየተደረገ ያለው ከሕዝብ ጥያቄ በመነሳትና ሕገ-መንግሥቱን መሠረት በማድረግ ነው»

*- አራርሳ መርዳሳ*
*የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጄነራል*

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ሰሞኑን የክልል ልዩ ኃይሎችን በተመለከተ የተለያዩ አስተሳሰቦች ሲሰነዘሩ ነበር። መንግሥት በበኩሉ በአገሪቷ ሊኖር የሚገቡ የጸጥታ ኃይሎች መከላከያ ሠራዊት፣ ፌደራል ፖሊስን እና የከተማ ፖሊስ መሆኑን ጠቁሟል።

በተለይም ለአንድ ሀገር ሕልውና መረጋገጥ ኅብረብሔራዊ የሆነ መከላከያ ሠራዊት መኖሩ ግዴታ ነው። ስለሆነም ይህንኑ ወደ ተግባር ለመቀየር በየክልሉ የሚገኙ ልዩ ኃይሎችን እንደገና የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑ በሰፊው ሲዘገብ ቆይቷል። ይህንን ለማሻሻልም እንደዚሁ በሞራል የተገባበት አለመሆኑና ሰፊ ጥናት ተደርጎበት ስለመሆኑም ተብራርቷል።

የልዩ ኃይል አደረጃጀት ብሔር ተኮር መሆን፤በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና የሌለው መሆኑና በተለይም የክልሎችን ሰፊ በጀት እየበላ ሰለሆነ ልዩ ኃይሎችን እንደገና ማደረጃት አስፈላጊ ሆኗል።

በዛሬው ዕትማችን የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጄነራል አራርሳ መርዳሳ በልዩ ኃይሎች የሪፎርም ሥራዎች፣ አካሄዶችን አሁናዊ ገጽታ ብሎም የክልሉን መፃዒ ሰላም ምን ሊሆን ይችላል በሚለው ላይ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ አድርገዋል። በተጨማሪም በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ሸኔን የመሳሰሉ ፀረ ሰላም ኃይሎች አካሄድ ስለሚገታበት መንገድም ምን መሆን ይችላል በሚለው ላይ ኮሚሽነር ጄኔራሉ የሰጡትን ምላሽ አዲስ ዘመን እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል።

**አዲስ ዘመን፡- የልዩ ኃይል ሪፎርም ማድረግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** ልዩ ኃይልን ሪፎርም የማድረጉ አስፈላጊነቱ ከመጀመሪያውኑ ጀምሮ ሲመሠረትና ሲደራጅ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ተከትሎ አይደለም። ሕጋዊ እና ሕገ-መንግሥታዊ መሠረት የለውም። እንደ አገር ተፈጥሮ በነበረው የሰላም ሁኔታ ሁሉም ክልሎች በየራሳቸው የየራሳቸውን ልዩ ኃይል ሲያደራጁ ቆይተዋል። ይህ ተሞክሮ በአንድ ክልል ተጀምሮ ሁሉም ክልሎች ደግሞ እንደ ነባራዊ ሁኔታ በየክልላቸው ያለውን ልዩ ኃይል አደራጅተዋል። ይህ ኃይል ከተደራጀ በኋላ ግን ሕዝቡ ጥያቄ ሲያነሳ ነበር። በተለይም በአንድ አገር ሁለት የታጠቀ ኃይል መኖር የለበትም ሲልም ነበር፤ መንግሥት የአገርን ዳር ድንበር በአገር መከላከያ ሠራዊት ማስጠበቅ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ መደበኛ ፖሊስ አለ። እንዲሁም ደግሞ የፌደራል ፖሊስም አለ። እነዚህ የጸጥታ አካላት አገርን መጠበቅ ይችላሉ። ይህ ሆኖ ሳለ እነዚህ ልዩ ኃይሎች ለምን አስፈለጉ የሚል ጥያቄ አስቀድሞም ቢሆን ሲነሳ ቆይቷል። በዚህም የተነሳ መንግሥት ጥናት አካሂዶ በቀጣይ ማስተካከል እንደሚችል በይደር የቆየ ጉዳይ ነው። ይሁንና አገሪቱ ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ብሎም ሸኔ እና ሌሎችን አሸባሪ ኃይሎችም ለመቆጣጠር በመደበኛ ፖሊስ ብቻ ስለማይቻል የሕግ መሠረት ባይኖረውም የክልሎችን ሰላም እና መረጋጋት ለማምጣት ብሎም ልማት ለማፋጠን እና ክልሎችን ለማረጋጋት ሲጠቀሙበት ነበር።

ይህ የሚያሳየው ነገር የሕዝብ ጥያቄ ትክክል መሆኑን ነው። ሀገር እየተረጋጋች ስትሄድ ደግሞ ይህ የተደራጀው ኃይል በጥናት ላይ ተመሥርቶ መስተካከል እንዳለበት የፌደራሉም ሆነ የክልል መንግሥታት በየጊዜው ሲወያዩበት ነበር። የኦሮሚያ ፖሊስም መንግሥት በሰጠው አቅጣጫ መሠረት መስተካከል እንዳለበት ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ሪፎርም ማድረጉ ለምን አስፈለገ? ለሚለው የመጀመሪያው ከአመሠራረቱ ጀምሮ በሀገሪቱ ሕግና ሕገ-መንግሥትን መሠረት አድርጎ ባለመሆኑ ነው ሪፎርም ማድረግ ያስፈለገው። ሁለተኛው ደግሞ ይህ ኃይል መስተካከል እና ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆን አለበት። መደበኛው ፖሊስ ለሕዝቡ በቂ ጥበቃ



ማድረግ አለበት። በመሆኑም የክልል ልዩ ኃይሎችን በተመለከተ የክልል መንግሥታት ኃላፊነቱን ወስደው በሥራ ላይ እያዋሉት ነው። እነዚህን አካላት ከሕግ ጋር ለማስተሳሰር ታስቦ የተገባበት ነው። ጥፋት ሲኖር ደግሞ እንደየሁኔታው የአገር መከላከያ ሠራዊት፣ ፌደራል ፖሊስ እና የክልል መደበኛ ፖሊሶች በመኖራቸው መቆጣጠር ይቻላል። በአጠቃላይ ይህ ሪፎርም እየሆነ ያለው ከሕዝብ ጥያቄ በመነሳትና የሕገ-መንግስቱን አንቀጾ እሳቤን መሠረት በማድረግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ አካላት እየተደረገ ያለው አካሄድ ሪፎርም ሳይሆን ልዩ ኃይልን ማፍረስ ነው ይላሉ። እውነታው ይህ ነው?**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** ይህ ማፍረስ አይደለም። አንዳንድ አካላት ከጥላቻ የተነሳ ይህን ይላሉ። ሐሳቡን እና ዓላማውን በአግባቡ ካለመረዳት የተነሳም ነገሩን በማንሸዋረር የሚረዱ ሊኖሩ ይችላሉ። እነርሱ እንደሚሉት ማፍረስ የሚባል ነገር የለም። እየተደረገ ያለው ሪፎርም ነው። ማፍረስ የሚባለው እና ሪፎርም እየተደረገ ነው ማለት ይለያያሉ። እነዚህን ኃይሎች መልሶ ማደራጀት እና ሪፎርም ማድረግ ወይም መሥራት ነው። ልዩ ኃይሉ አሁን በተደራጀበት ሁኔታ መቀጠል አይችልም።ሕገ መንግሥታዊም አይደለም።

ይህ ኃይል ትናንት ክልሎችን ሲያረጋጋ ነበር። ይህ ኃይል ለሕዝብ ሲል ሲሞት እና ሲቆስል ነበር። ይህ ኃይል ትልቅ ዋጋ የከፈለ ነው። ይሁንና የተመሠረተበት አካሄድ በሕግ አግባብ ሲታይ ትክክል አይደለም። በሕገ መንግሥቱ የተመሠረተም አይደለም።

አደረጃጀቱ ከሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ጋር መጣጣም አለበት። በመሆኑም ይህ ኃይል እንደገና መደራጀት አለበት። ስለዚህ ይህ ኃይል በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የአገር መከላከያ ሠራዊትን መቀላቀል የሚፈልግ ወደ አገር መከላከያ ሠራዊት ይቀላቀላል። ፌደራል ፖሊስ ውስጥ መካተት የሚፈልግ ደግሞ ወደ ፌደራል ፖሊስ እንዲካተት ይደረጋል። ወደ መደበኛ ፖሊስ መቀላቀል የሚፈልግም በተመሳሳይ ወደ መደበኛ ፖሊስ እንዲቀላቀል ነው የሚደረገው። በዚህ ውስጥ መታቀፍ የማይፈልግ ደግሞ ድጋፍ ተደርጎለት በቀዬው መቋቋም የሚችልበትን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። ስለዚህ

> **የተደራጀ እና አስቺጋሪ ኃይል ሥርዓት የሚያስይዝ፣ የአገርን ዳር ድንበር የሚጠበቅ የአገር መከላከያ ሠራዊት ነው። የፌደራል ፖሊስ በተመሳሳይ በሀገር ውስጥ የራሱ ተልዕኮ አለው**

ሪፎርም ማድረጉ እነዚህን ነገሮች ታሳቢ ያደረገ ነው። ከዚህ በዘለለ ግን ማፍረስ የሚለው በተደረገው ጥናት እና እየሆነ ካለው ነገር ጋር የሚጣጣም ሐሳብ አይደለም። እየተደረገ ያለው አደረጃጀት የሀገሪቱን ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ለሀገሪቱ ሕዝብና መንግሥት የበለጠ ግልጋሎት የሚሰጥበትን መንገድ መከተል ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ አሁን እየተሄደበት ያለው መንገድ አመቺ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሚታጠቁት የጦር መሣሪያ አኳያም ብዙ ብዥታዎች አሉ። በዚህ ላይ ግልጽ የሆነ ነገር አለ?**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** ከሚታጠቁት የጦር መሣሪያ ጋር ተያይዞ ለመደበኛ ፖሊስ፣ አዲስ ለሚደራጀው እና ለእያንዳንዱ መዋቅር ስታንዳርድ አለው። በተለይም የቡድን የጦር መሣሪያዎችን በተመለከተ እና ከመደበኛ ፖሊስ ስታንዳርድ በላይ ከሆነ የሀገር መከላከያ ሠራዊት የሚታጠቀው ይሆናል። የተደራጀ እና አስቸጋሪ ኃይል ሥርዓት የሚያስይዝ፣ የሀገርን ዳር ድንበር የሚጠበቅ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ነው። የፌደራል ፖሊስ በተመሳሳይ በሀገር ውስጥ የራሱ ተልዕኮ አለው። አሸባሪዎችን መቆጣጠር፣ ሀገር ውስጥ ደህንነት እና ሰላም ማስከበር እና የመሳሰሉትን የፌደራል ፖሊስ ያስከብረዋል። ከዚህ በላይ ከሆነ ደግሞ የሀገር መከላከያ ሠራዊት እርምጃ ይወስዳል። መደበኛ ፖሊስም የራሱ የሆነ ኃላፊነት ይኖረዋል።

ስለዚህ ሁሉም እንደየደረጃውና አስፈላጊነቱ አገልግሎት ይሰጣሉ። መደበኛ ፖሊስም ከሚሊሻ ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ በአሠራር ምላሽ የሚያገኙ ይሆናል። ስለዚህ አንዳንድ አካላት ልዩ ኃይልን ለማፍረስ እየተሠራ ነው የሚለው አግባብ አለመሆኑን መገንዘብ እና ይልቁንም መልሶ ማደራጀትና የሕግ አግባብ ያለው መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ይህን የሚያራግቡ አካላትም እውነታውን ቢረዱት መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ኦሮሚያ ክልል በጉዳዩ ላይ ያለው መረዳት ምን ይመስላል?**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** እንደ አሮሚያ ክልልም በዚህ ላይ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ውይይት አድርገውበታል። በዚህ ላይም የልዩ ኃይል አደረጃጀት ከሀገሪቱ ሕገ መንግሥት አኳያ ድጋፍ የሌለው መሆኑንና ይህን ኃይል እንደገና መልሶ ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን የልዩ ኃይል አመራሮች ጨምሮ ምክክር ተደርጎበታል። ከአባላቱም ጋር በተደረገው መግባባት እንደየፍላጎታቸው እና ችሎታቸው በሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ በፌደራል ፖሊስ ወይም ደግሞ በመደበኛ ፖሊስ መካተት የሚችሉበት ሁኔታ ስለመኖሩ ታምኖበታል። አባላቱም ተመዝግበው ወደ ሥራ ለመግባት ሂደቶች በመጠናቀቅ ላይ ናቸው። ይሁንና ይህን ነገር የሚያወናብዱት በብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መካከል መጠራጠር እንዲነግስ ነው።

ልዩ ኃይልን የማደራጀቱ ሥራ ላይ ውዥንብር የሚፈጥሩ አካላት አይጠፉም። የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ትጥቅ እንዳልፈታ በማስመሰል የሚናፈሱ ወሬዎች አሉ። ነገ ወሬኞች እንደለመዱት አፋቸውን መያዛቸው የሚቀር ባይሆንም ሠራዊቱ ትጥቁን ይዞ ወደ ካምፕ እየገባ እና እየሰለጠነ መሆኑን ሕዝብ እየተመለከተው ነው። ስለዚህ በሕዝቦች መካከል መጠራጠር እንዲኖር ማድረግ ተገቢ አይመስለኝም። በእርግጥ አንዳንዶች በሶሻል ሚዲያ እና ከኋላ ሆነው የሚያራግቡ ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል።

እውነታው ግን የፌደራል መንግሥት ጥናት አካሂዶ እንደ ሀገርም የተወሰነ ጉዳይ ነው። የተሰጠው አቅጣጫም ሁሉም ክልሎች ተግባር ላይ እንዲያውሉት ነው። በመሆኑም ኦሮሚያ ውስጥ የሚተገበር በአማራ፣ አፋር፣ ጋምቤላ እና ሌሎች ክልሎችም እየተተገበረ የሚሄድ ይሆናል። እኛ እንደ ኦሮሚያ ክልል በተሰጠን አቅጣጫና ጊዜ መሠረት ሥራውን እናጠናቅቃለን። ከዚህ ባለፈ ግን ያልተጨበጠ ወሬ እና ውሸት ፈብረከው የሚያወናብዱት አካሄዳቸውን ማየት አለባቸው። የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች እና ባለሙያዎችም ይህን በሚገባ ለሕዝቡ ማሳወቅና ማስገንዘብ አለባቸው።

በብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ክልሎች መካከልም የተለያየ አሠራር የተፈጠረ አለመሆኑንም ማሳየት ተገቢ ነው። ከዚህ ውጭ ትናንት ይህ ኃይል ከአመሠራረቱ እና ከሚታጠቀው የጦር መሣሪያ ጭምር ሕገ-መንግሥታዊ መሠረት የለውም፤ መፍረስ ይኖርበታል ብለው ሲሞግቱ እና ሲከራከሩ የነበሩ አካላት በአሁኑ ወቅት ደግሞ የክልል ልዩ ኃይሎች መፍረስ የለባቸውም በሚል ቅስቀሳ መጀመራቸው ነጭ ውሸት እየዋሹ በመሆኑ ማወቅ ተገቢ ነው።

ዓላማው በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬ ማንገሥ እና አንዱ ከሌላው ጋር ባለው ግንኙነት እንዳይተማመን ማድረግ ነው።፣ ለሀገር እና ለሕዝብም ደንታ የሌላቸው አካላት የሚያደርጉት አካሄድ ነው። ሕዝብን ወይም ብሔርን እንደ ብሔር መርገም፣ መስደብ እና ማንቋሸሽ በዚህ ክፍለ ዘመን መኖር የሌለበት ነው። እነዚህ አካላት ምንም የማያውቁ ናቸው። ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት የነበረውን ጉዳይ አሁን የሚያወሩ አሉ።

ከሀገር ውጭ ሆነው ይህን የሚያራግቡት ጥቂቶቹ በወንጀል የሚፈለጉ ናቸው፤ ጥቂቶቹ ደግሞ ተለጣፊ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ


ወይም ጥገኝነት ፈላጊ ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ ከብሔር ጥላቻ የመነጨ ነው። እንደዚህ የሚጮኹ አካላትም ከዚህ ድርጊታቸው ቢታቀቡ መልካም ነው። በአጠቃላይ ግን እነርሱ እያወሩ ያሉት ውሸት ስለመሆኑ ሕዝባችን ያውቀዋል። ከዚህ በተረፈ የተሰጠንን ኃላፊነት በጊዜ አጠናቅቀን መንግሥትም የጣለብን ሀገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እና የመንግሥትን አቅጣጫ ሥራ ላይ በማዋል የሕዝብን ሠላምና መረጋጋት ለማረጋገጥ የምንሠራ ይሆናል። ሕዝባችንም እውነታውን በመገንዘብ እና እየሠራን ያለው ነገር በመመልከትም አጋዥ ኃይላችን ሆኖ እንዲቀጥል ማሳወቅ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ኦሮሚያ ክልል ልዩ ኃይሉን ወደ ሪፎርም እንዲገባ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን ሠላምና መረጋጋት ከማስጠበቅ አኳያ ምን ታስቧል?**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** በኦሮሚያ መጀመሪያ የነበረው ኃይል ፈጥኖ ደራሽ የሚባል ነበር። ተልዕኮውን አጠናቋል ተብሎ ወደ መደበኛ ፖሊስ እንዲቀላቀል ተደርጓል። ያኔ ሲመሠረት ልዩ ኃይል የሚባል አልነበረም። በኋላ ሁኔታዎች እንደተጠበቀው አልሆን በማለታቸው ተመልሶ ልዩ ኃይል ወደ ማደራጀት ተገብቷል። ያኔ የነበረው ኃይል አመሠራረት፣ አካሄድ ብሎም ዓላማው ከአሁኑ ጋር ይለያያል።

እንግዲህ በአሁኑ ወቅት እንደ ኦሮሚያ ክልል ለሠላምና ደህንነቱ ስጋት የሚሆነው በዋናነት ሸኔ ነው። በአሁኑ ወቅትም በኦሮሚያ አዋሳኝ አካባቢዎች ሰላምን የሚያውኩ አካላትም አሉ። እንደ ኦሮሚያ ክልል መንግሥት ለሸኔ የሰላም ጥሪ አቅርቧል። እንደ እኛም ይህን ጥሪ ተቀብሎ የሚገቡ ከሆነ ሰላምና መረጋጋት እንደሚመጣ እምነት አለን። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን በዋናነት ኃላፊነት የወሰደው የሀገር መከላከያ ሠራዊት ከአካባቢ ሚሊሻዎች እና ፖሊሶች ጋር በመሆን ጠራርጎ ማስተካከል እንደሚችል አንዳች ጥርጣሬ የለንም።

እንድ ኦሮሚያ ክልልም ልዩ ኃይሉ ሪፎርም ስለተደረገ



በሕዝባችን ላይ ችግር ይደርሳል ብለን አንሰጋም። የፌደራል መንግሥት ዝግጅት አድርጓል። በሰላማዊ መንገድና በድርድር ካልሆነ በስተቀር በአፈሙዝ የሚገኝ ሥልጣን እንደሌለ ግልጽ አቅጣጫ አለ።

ሥልጣን የሕዝብ ነው። ሕዝብ ደግሞ ያመነበትን በካርድ ይመርጠዋል። ሥልጣን የሚገኘው በዚህ መንገድ ነው። ስለዚህ መንግስት ያቀረበው ሠላማዊ ጥሪ አለ። ይህን ጥሪ ተቀብሎ የሚመጣ ካለ በሰላማዊ መንገድ መንቀሳቀስ ይችላል። ይህን የማይቀበል ኃይል ካለ በሕዝባችን ላይ ስቃይ ማብዛት የለበትም፤ አስፈላጊ እርምጃ ይወሰድበታል። ስለዚህ የልዩ ኃይል ሪፎርም በመደረጉ እንደ ኦሮሚያ ክልል የሚፈጥረው ሥጋት የለም ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኦሮሚያ ክልል የተፈጠረው ችግር የኦሮሚያ ችግር ብቻ ሳይሆን የሁሉም ነው፤ ስለዚህ ሰው በሰላም ወጥቶ እንዲገባ ምን የታሰበ ነገር አለ?**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** የተለያዩ ጸረ ሰላም ኃይሎች አሉ፤ በተለይም እነዚህ አካላት በሚዲያ ላይ እንደምታየው ሕዝብን ግደል፤ አሳድድ እያሉ ሕዝቡን በጎ ላልሆነ ተግባር የሚያነሳሱ እና አንዱ በአንዱ ላይ እንዲያምጽ የሚያደርጉ ናቸው። ስለዚህም እነዚህን ኃይሎች የፌዴራል ኃይል መስመር ለማስያዝ እንቅስቃሴ ጀምሯል።

ማንኛውንም ጸረ ሰላም ኃይል ፖሊስ አደብ የማስገዛት ኃላፊነት አለበት። ነገር ግን ፖሊስ ከአቅሙ በላይ ከሆነ ደግሞ ተጨማሪ ኃይል ሊጠየቅ ይችላል። እንደሚታወቀው ደግሞ ከጅምሩ ሲታይ ፖሊስ የሕዝብን ሰላም ለማስጠበቅ እና በነጻነት የመንቀሳቀሱን ነጻነት ለማረጋገጥ የሚሠራው ነው። ዋና ኃላፊነቱም የሕዝብን ሰላም ማረጋገጥ ነው። ፖሊስ ራሱን መስዋዕት በማድረግ ሕዝቡ በሰላም እንዲወጣና እንዲገባ ማድረግ ነው። ከሰፈር ተነስቶ እስከ ወረዳና ክልል ደረጃ ድረስ ያለ አደረጃጀትም ሲታይ የሚያመላክተው ይኸው ነው።

በተለይ ደግሞ ከሕዝብ ጋር ትስስር ፈጥሮ በመሥራት ሰላም ፈላጊውን ሕዝብ መጠበቅ ዋና ተግባሩ ነውና የሚሠራውም እዚሁ ላይ ነው። ሰላም ፈላጊውን ሕዝብ በማደራጀት ሰላም የማይፈልጉትን ከመካከላቸው እንዲያወጡ በማድረግም ሰላም እንዲሰፍን የሚያደርግ ኃይል ነው። በተለይ ደግሞ ሰላም የማይፈልገውን አካል ኃይል እንዳይኖረው የሚቆጣጠር ነው። ከዚህ አኳያ የሕዝብን ሰላም ለማስከበር አጠናክሮ የሚሠራ ይሆናል።

በመንግስት የተደረገውን ጥሪ ወደጎን በመተው የጦርነትን ነጋሪት የሚጎስሙትን ጸረ ሰላም ኃይሎች መንግሥት ትኩረት በመስጠት መስመር የሚያስይዛቸው ይሆናል። ከዚያ በኋላ እነዚህ ጸረ ሰላም ኃይሎች ባያያዙት እሳት ደግሞ ራሳቸው እንደሚቃጠሉ ምንም ጥርጥር የለውም። እነሱ ያደረጉት ጥሪ ይህን ሀገር የማፍረስ ጥሪ ነው። ሕዝቡንም የማደነጋገርና የማፍረስ ጥሪ ነው። ይህ ሕዝብ አንድ ሆኖ በሀገሩ እንዳይኖር የሚያደርግ ጥሪ በመሆኑ ይህ የማይሆንና የማይሳካ ሕልም ነው ብዬ እወስደዋለሁ።

ይህን ያደረጉ አካላት ደግሞ በታሪክም በሕግም ይጠየቁበታል ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ ይህን ያደረገው አካል በተለያየ ቦታ ያለውን ሕዝብ በማፈናቀል እና ሕዝቡ እንዲሰቃይ በማድረጉ በኩል እያደረጉ ያለው አካሄድ በታሪክም በሕግም የሚጠየቁ ስለመሆናቸው እርግጥ ነው። ይህ ጊዜ ደግሞ ሩቅ አይሆንም። ሕዝብ በማሰቃየቱ ረገድ እያደረጉ ባሉት ሴራም የሚጠየቁ ይሆናል። እርምጃም የሚወሰድ ይሆናል።

ከዚህ አኳያ በዚህች ሀገር ከሕግ በላይ የሚሆን አካል ይኖራል ብዬ አላምንም። ካለም የሚሆነው የጊዜ ጉዳይ ነው፤ ጊዜው እስከፈቀደለት ሊኖር ይችል ይሆናል። ምክንያቱም ሕዝብ ነው ዋናው። በሕግ ተገዝቶ እንጂ ማንም ጉልበቱን ተማምኖ እንደልቡ መኖር አይችልም። በተለይ ደግሞ ሕዝብ ከመረጠው ተመራጭ ውጪ በጉልበት የሚመጣ አካል የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ቀጣይነትም አይኖረውም።

ሕዝቡን የሚያሰቃዩ፣ ሥልጣን ፈልገው ባለሥልጣናትን የሚያሳድዱ በሀገር ደረጃም ሆነ በሌላው የዓለም ክፍል ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ከሕግ ውጭ የሆነ ሁሉ ቀጣይነት ስለማይኖረው በአጭር የሚቀር ነው። ይህ ትርፍ የሌለውም አካሄድ ነው። ለዚህች ሀገር መረጋጋት ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መመካከር የግድ ይላል። ነገር ግን ሕዝብን ማስቸገርና ሕዝቡ ስጋት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የሚኬድ ከሆነ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎችም ይሁኑ ሌሎች ግለሰቦች ተጠያቂ የሚሆኑበት ጊዜ ቅርብ ይሆናል። መንግሥትም ይህንኑ ነው አጠናክሮ የሚሠራው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን መረጃ በእጅጉ አመሰግናለሁ።**

**ኮሚሽነር አራርሳ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።


## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በ2015 በጀት አመት ሃአግ/ኢቴፋቴኢ ግዥ/515/2015 የኮምፒዩተር እና ተዛማጅ እቃዎች በግልጽ ጨረታአወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለዚህ በጨረታው ለመካፈል የሚፈልጉ እና ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች እንዲወዳደሩ ይጋብዛል።

1. በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ድረ-ገጽ የተመዘገቡ፣ ያለማጭበርበሩ ፎርም ላይ መሀተምና ፊርማ የተደረገበት፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር TIN፣ የተጨማሪ እስቴት ታክስ ማስረጃ ፣ የዘመኑን የሥራ ግብር የከፈሉበትና የግብር ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ የሚችሉ ሆነው የሁሉንም የፋይናንሻል እና የቴክኒካል ሰነዶቻቸውን ኮፒና ኦርጅናል ከጨረታ ሰነዱ ጋር በአግባቡ ታሽጎ በተለያየ ፖስታ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
2. ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማይመለስ 200.00/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ሰነዱን መግዛት የሚችሉ ሲሆን ሰነዱን ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት ግዥ ክፍል መግዛት ይችላሉ።
3. በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጅ መሰረት የተቋቋሙበትን የህጋዊነት ማስረጃ ዋናውን እና የማይመለስ ኮፒውን በማሳየት ያለ ክፍያ በነጻ የጨረታ ሰነዱን ማግኘት ይችላሉ።
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 100,000.00/አንድ መቶ ሺህ ብር/በባንክ በተረጋገጠ CPO፣ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ ወይም በጥሬ ገንዘብ ማቅረብ የሚፈልጉ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት GOV1000096185007 በኢትጵያ ንግድ ባንክ ገቢ በማድረግ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኙን በመክፈቻው ሰዓት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
5. በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የጨረታ ማስከበሪያ በማቅረብ ምትክ ተቋማቱን ከአደራጀው አካል የሚሰጥ የዋስትን ደብዳቤ ማቅረብ ይችላሉ።
6. አሸናፊው ድርጅት ያሸነፈባቸውን እቃዎች አሸናፊነቱ ታውቆ ውል ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በውሉ መሰረት ማቅረብ የሚችል መሆን ይጠበቅበታል።
7. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በመግለጽ በታሸገ ፖስታ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት ግዥ ክፍል በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።
8. ሃአግ/ኢቴፋቴኢ ግዥ/515/2015 ኮምፒዩተር እና ተዛማች እቃዎች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ቀን 4፡30 ይከፈታል።
9. ኢንስቲትዩቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
10. በሌላ ተጫራች ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም።
11. ጨረታው የሚከፈትበት ቀን ቅዳሜ እና እሁድ ወይም ካላንደር የሚዘጋው የበዓላት ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ጨረታው የሚከፈት ይሆናል።

**ማሳሰቢያ፡-** ተጫራቾች አላስፈላጊ ድርጊት ላለመፈጸም ቃል የሚገቡበትን ቅጽ ሞልተውና ፈርመው ከመወዳደሪያ ሰነዱ ጋር ለመመለስ ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0588304419 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።

**የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት**

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# በተስፋና በስጋት መካከል የቆመው የቆዳ ዘርፍ

**አንተነህ ቸሬ**

ኢትዮጵያ በርካታ የቀንድ ከብት ሀብት ካላቸው አገራት መካከል ትመደባለች። ይህ የቀንድ ከብት ሀብት ባለቤትነቷ በቆዳ ልማት ዘርፍ ትልቅ አቅም እንዲኖራት አስችሏታል። ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉት ከዘርፉ የሚገኙት ብዙዎቹ ምርቶች ከአገር ውስጥ ገበያ ተሻግረው በውጭ አገራት ገበያዎችም ተፈላጊ ናቸው።

በቆዳ ልማት ዘርፍ ባለፉት 20 ዓመታት፣ በተለይም በቆዳ ላይ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ የማቅረብ ስርዓት /የተጨማሪ እሴት አሰራር ስርዓት/ መተግበር ከተጀመረ ወዲህ፣ በርካታ አወንታዊ ለውጦች ማስመዝገብ እንደተቻለ የዘርፉ አካላት ይገልጻሉ።

እንዲያም ሆኖ ግን በቆዳ ልማት ዘርፍ እምቅ አቅም ያላት ኢትዮጵያ ከዘርፉ የምታገኘው ጥቅም እዚህ ግባ የሚባል አይነት አይደለም፤ ይህን እምቅ አቅም ተጠቅሞ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ትልቅ ስራ የሚጠይቅ ሆኖ ይስተዋላል። በእርግጥ አገሪቱ በዘርፉ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ባለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራትን ማከናወኗ አይካድም፤ ይሁንና በቁጥርም በዓይነትም የበዙት የዘርፉ ችግሮች ተጨማሪ ጥረቶችን የሚጠይቁ ናቸው።

ከአገሪቱ አቅም አንፃር የቆዳ ልማት ዘርፍ ከፍተኛ እድገት ማስመዝገብ የሚችልበት እድል እንዳለው ቢታመንም በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ማምረት ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች ግን በርካታ ችግሮች እንዳሉባቸው በተደጋጋሚ ይገለፃል። ኋላ ቀር የከብት እርባታ ስልት፣ ጥራት የጎደለው የእርድ ተግባር፣ የቆዳ አያያዝና አመራረት፣ ደካማ የግብይት ቁጥጥር ስርዓት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውስንነት እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ እጥረት በቆዳ ዘርፍ እድገት ላይ አደጋ ከደቀኑ መሰናክሎች መካከል ይጠቀሳሉ።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ የኢትዮጵያ የቆዳ ልማት ዘርፍ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ችግር አጋጥሞታል። የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትና የግብዓት ችግሮች በዘርፉ ህልውናና እድገት ላይ ከፍተኛ አደጋ ደቅነዋል። ከአምስት ዓመታት በፊት በዓመት 133 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ያስገኝ የነበረው ይህ ዘርፍ፣ ባለፈው ዓመት ግን ከዘርፉ የተገኘው የወጪ ንግድ ገቢ 40 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነው። ከውጪ ንግድ ገቢው መቀነስ በተጨማሪ በዘርፉ የተሰማሩ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ለከፍተኛ ችግር ተዳርገዋል፤ አንዳንዶቹ በዝቅተኛ አቅም እያመረቱ ሲሆን ብዙ አምራቾች ደግሞ የምርት ስራቸውን ለማቆም ተገድደዋል።

በቆዳ ማልፋትና ማለስለስ እንዲሁም የቆዳ ውጤቶችን በማምረት ላይ የተሰማሩ አምራቾች አብዛኛው ስራቸው ከውጭ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ብዙዎቹ ፋብሪካዎች የገበያ ስምምነታቸውን መሰረት በማድረግ ለመስራት የሚያስችላቸው ሁኔታ የለም። የመንግሥትና የአምራቾች የውጭ ምንዛሬ መጋራት የድርሻ አሰራር 50/50 እንዲሆን በተደጋጋሚ ቢጠየቅም 20/80 ሆኖ እንደቀጠለ ነው። ይህ አሰራር ደግሞ ግብዓቶችና መለዋወጫዎችን በበቂ ሁኔታ ለማግኘት መሰናክል ሆኗል።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር ዋና ጸሐፊ አቶ ሰለሞን ጌቱ፣ ኢትዮጵያ በቆዳው ዘርፍ ያላት አቅም አገሪቱ ባላት የከብት ሀብት ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነ ይናገራሉ። «የኢትዮጵያ የቆዳ ሀብት በብዛት ከመገኘቱ በተጨማሪ በርካታ ልዩ ባህርያት ያሉትም ነው። የቆዳው የተፈጥሮ ጥራት ዋጋው ውድ እንዲሆን በማድረግ ከፍ ያለ ገቢ ለማግኘት ይረዳል። ዘርፉ ከፍተኛ የመልማት እንዲሁም በውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ በስራ እድልና በሀብት ፈጠራ ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት ትልቅ አስተዋፅዖ የማበርከት አቅም አለው። የቆዳ ዘርፍ በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ የሚፈጥረው ሀብት ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ቆዳ የሚያስገኘው የተጨማሪ እሴት ጥቅም ሌሎች ዘርፎች ከሚያስገኙት የበለጠ ነው» ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፣ ብዙ አገራት በቆዳ ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ፈጥረው ራሳቸውን የሚጠቀሙበት ደረጃ ዝቅተኛ ነው ከአንድ በመቶ አይበልጥም። ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ አገራት ላለፉት ዓመታት ቆዳ ሀብት እንዲፈጥር ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን አከናውነዋል። በኢትዮጵያ ተግባራዊ የተደረገው የተጨማሪ እሴት ፖሊሲ/በቆዳ ላይ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ የማቅረብ ስራ/ለውጥ አምጥቷል።

**በቆዳ ማልፋትና ማለስለስ እንዲሁም የቆዳ ውጤቶችን በማምረት ላይ የተሰማሩ አምራቾች አብዛኛው ሥራቸው ከውጭ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ የተመሰረተ ነው። ብዙዎቹ ፋብሪካዎች የገበያ ስምምነታቸውን መሰረት በማድረግ ለመሥራት የሚያስችላቸው ሁኔታ የለም። የመንግሥትና የአምራቾች የውጭ ምንዛሬ መጋራት የድርሻ አሰራር 50/50 እንዲሆን በተደጋጋሚ ቢጠየቅም 20/80 ሆኖ እንደቀጠለ ነው። ይህ አሠራር ደግሞ ግብዓቶችና መለዋወጫዎችን በበቂ ሁኔታ ለማግኘት መሰናክል ሆኗል**




ፖሊሲው የአምራቾች ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል። አምራቾች የምርት ዓይነትም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ በመሆኑ ምርቶቹ በውጭ አገራት ገበያዎች ጭምር በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ መሆን ችለዋል።

ይሁን እንጂ ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና ትክክለኛ የገበያ ትስስር ተጠቅሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ አገሪቱን ለመጥቀም ብዙ ስራዎች እንደሚቀሩ አቶ ሰለሞን ያስረዳሉ። የኮቪድ ወረርሽኝ፣ የሰሜኑ ጦርነትና በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች የተፈጠሩ አለመረጋጋቶች በቆዳ ዘርፍ ልማት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን እንዳሳደሩ ዋና ፀሐፊው ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው እርድ በቤት ውስጥ መከናወኑ ጥራቱን የጠበቀ ቆዳና ሌጦ የማግኘቱን ስራ አስቸጋሪ እንዳደረገው ጠቁመው፣ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት ጉድለት፣ በተለይም እየተባባሰ የመጣው የቆዳ መቀደድና የቅርፅ መበላሻት፣ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚፈልግም ያመለክታሉ።

አቶ ሰለሞን ኢንዱስትሪው መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚያስፈልገውም ይጠቁማሉ። «ቆዳ አምራቾች አዋጭ በሆነ መልኩ በአንድ ቦታ ተሰብስበው እንዲሰሩ ማድረግ (Clustering) ያስፈልጋል። ይህም ተረፈ ምርቶች ወደ ገንዘብ የሚቀየሩበትን እድል እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃና ለተወዳዳሪነትም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።» ሲሉ ጠቁመው፣ የትልልቅ ብራንዶች ወደ ገበያው መግባትም በቆዳ ኢንዱስትሪዎች አንድ አካባቢ መሰባሰብ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይናገራሉ። ሌሎች የአፍሪካ አገራት የሌዘር ፓርኮችን እየገነቡ እንደሚገኙ አመልክተው፣ በዚህም የኢትዮጵያን ገበያ ወደራሳቸው መውሰድ ይፈልጋሉ። ትልልቅ አምራቾች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ከተበታተነ አሰራር መውጣት ስንችል ነው» ሲሉ ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ሬድማን በዳዳ በበኩላቸው፣ የቆዳው ዘርፍ ብዙ ችግሮች ያሉበት እንደሆነ ገልፀው፣ ማኅበረሰባዊ የግንዛቤ ለውጥ እና የመንግሥት ቁርጠኝነት ለችግሮቹ መፍትሄዎች እንደሚሆኑ ይናገራሉ። «ቀደም ባለው ጊዜ የቆዳ ዘርፍ ከቡና ቀጥሎ ትልቁ የኢኮኖሚ ዋልታ ነበር። በቅርብ ጊዜያት ዘርፉ በኮቪድ ወረርሽኝ እና በውስጣዊ ችግሮች ምክንያት ተቀዛቅዟል። መንግሥት የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ አለበት።» ሲሉ ያስገነዝባሉ።

የ20/80 አሰራር ስርዓት ለዘርፉ እድገት ምቹ እንዳልሆነና መሻሻል እንዳለበት ጠቅሰው፣ ተገቢ የውጭ ምንዛሬ ምደባ ሊኖር እንደሚገባ ይገልጻሉ። አምራቾች ከወጪ ንግድ ከሚያገኙት ገቢ ለግብዓትና ለመለዋወጫ ግዢ መጠቀም እንዲችሉ ሊፈቀድላቸው እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የቆዳ ዘርፍ ከፋይናንስ ተቋማት እያገኘ ያለው ገንዘብ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። በቂ የፋይናንስ አቅርቦት ያላገኘ ዘርፍ እድገት ሊያስመዘግብ እንደማይችልም ተናግረው፣፣ የፋይናንስ ተቋማት ለዘርፉ በቂ የብድር አቅርቦት ማመቻቸት እንደሚጠበቅበት አስታውቀዋል።

የቆዳውን ዘርፍ ለማነቃቃት ያስችላሉ ተብለው ተስፋ ከሚጣልባቸው ተግባራት መካከል በዘርፉ ተዋንያን መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶችን የሚያጠናክሩ መድረኮችን ማዘጋጀት አንዱ ነው። ይህን መሰረት በማድረግም የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማኅበር ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከተባበሩት መንግስታት የኢንዱስትሪ ልማት ድርጅት (UNIDO) እና ሌሎች አጋር ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው 13ኛው «የመላ አፍሪካ የቆዳ ትርኢት» ከዛሬ፣ ሚያዝያ 12 ቀን እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ፣ ሚሊኒየም አዳራሽ፣ ይካሄዳል። ላለፉት 15 ዓመታት በየዓመቱ ሲካሄድ የቆየው ይህ ትርኢት፣ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራቾችን፣ ሻጮችን፣ ገዥዎችን፣ ባለሀብቶችን፣ የቆዳ ቴክኖሎጂ አቅራቢዎችን፣ ተመራማሪዎችን፣ የፋይናንስ ተቋማትንና ሌሎች የቆዳ ዘርፍ ተዋናዮችን የሚያገናኝ ትልቅ አህጉራዊ የንግድ መድረክ ነው።

በዘንድሮው የንግድ ትርኢት ላይ ከ200 በላይ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አምራቾች፣ ግብዓትና ሎጂስቲክስ አቅራቢዎች፣ የቴክኖሎጂና የፋይናንስ ተቋማት እንደሚሳተፉ ይጠበቃል። ከ15ሺ በላይ የአገር ውስጥና ከሁለት ሺ በላይ የውጭ አገራት ጎብኚዎችም ትርኢቱን ይጎበኙታል።

«ትርኢቱ አፍሪካን ከቀሪው ዓለም ጋር የሚያገናኝ ጠቃሚ የንግድ መድረክ ነው» የሚሉት የማኅበሩ ዋና ፀሐፊ አቶ ሰለሞን፣ «መድረኩ ከኮቪድ-19 ተፅዕኖ እና ከዓለም አቀፍ የገበያ ስርዓት ውድቀት በኋላ የቆዳ ኢንዱስትሪን ለማነቃቃት እና የቆዳውን ዘርፍ ውድቀት ለመቀልበስ ትልቅ ሚና ይጫወታል። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የኢትዮጵያን ምርቶች ያስተዋውቃል፤ ሻጪና ገዢን ያገናኛል» ይላሉ። አቶ ሬድማንም የንግድ ትርኢቱ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለመለወጥ አወንታዊ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ይናገራሉ።

መንግሥት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል በቅርቡ ይፋ የተደረገው የ«ኢትዮጵያ ታምርት» አገራዊ ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው። የአገራዊ ንቅናቄው ዋና ዋና ዓላማዎች የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግሮች በጋራ በመፍታት ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማስቻል እንዲሁም በዘርፉ ያለውን የስራ ባህል ማሻሻል ብሎም የኢንዱስትሪ ምርቶችን ጥራትና ተወዳዳሪነት በማሻሻል ገቢ ምርቶችን የመተካት ሽፋንን ማሳደግ ናቸው።

ንቅናቄው የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ብሎም የዘርፉን ልማት ለመደገፍ እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪዎችን በጥራትና በቁጥር ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑበት ሲሆን የኢንዱስትሪ ዘርፉን ከተለመደው አሰራር በማሻገር ምርታማነትን ለመጨመር እንደሚያግዝ ታምኖበታል። በአሁኑ ወቅት ኢንዱስትሪዎች ለአገር ውስጥ ምርት እድገት እያበረከቱት ያለውን አነስተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያሳድግም ተስፋ ተጥሎበታል።

በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር የዘርፉን የማምረት አቅም ማሳደግ፣ ለዜጎች ተጨማሪ የስራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እና ገቢ ምርቶችን በአገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን ማዳን ከ«ኢትዮጵያ ታምርት» መርሃ ግብር የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል የ«ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ ኢንዱስትሪዎች የገጠሟቸውን ችግሮች በመፍታትና ለምርታማነታቸው ማደግ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የኢንዱስትሪው ዘርፍ በአገራዊ ኢኮኖሚ የሚኖረውን ድርሻ ለማሻሻል ታቅዶ መተግበር እንደተጀመረ በንቅናቄው ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ መግለፃቸው የሚታወስ ነው።

ንቅናቄው በቀጥታ ከሚመለከታቸውና ችግሮቻቸውን እንደሚያቃልልላቸው ከሚጠበቁት ዘርፎች መካከል አንዱ የቆዳ ዘርፍ ነው። ንቅናቄው በስራ እድል ፈጠራም ሆነ በገበያ ተወዳዳሪነት በተለይ ለቆዳ ልማት ዘርፍ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ተስፋ ተደርጎበታል።

ከንቅናቄው መጀመር በኋላ በዘርፉ የታዩት ለውጦች ይህን ተስፋ ወደ ተግባር የቀየሩ አወንታዊ እርምጃዎች እንደሆኑ አቶ ሰለሞን ይናገራሉ። «ኢትዮጵያ ታምርት ከቆዳው ዘርፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ንቅናቄ ነው። የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር እና የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነትም ለቆዳው ዘርፍ ትልቅ ብስራቶች ናቸው ሲሉ ይገልጻሉ።

ዘርፉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ለሚገኙ ተማሪዎች በሁለት ዙር ከ600ሺ በላይ ጫማ ማቅረቡን ጠቅሰው፣ ይህም በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት በእጅጉ ተቀዛቅዞ የነበረውን ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲነቃቃ አድርጎታል ነው ያሉት። በቀጣይም 800ሺ ጫማዎችን ለማቅረብ እየተሰራ መሆኑን ገልጸው፣ ትንንሽ አምራቾችን በማጣመር አቅም እንዲፈጥሩ በማድረግ ለማምረት ጥረት ተደርጓል ይላሉ። የአገር መከላከያ ሰራዊትና የፖሊስ አባላትን ጫማ በአገር ውስጥ ማምረት ተችሏል፤ በዚህም በርካታ የሥራ እድል መፍጠርና ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ማዳን መቻሉን አስታውቀዋል። ወደፊትም ብዙ አዳዲስ የሥራ እድሎችን እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

የቆዳ ዘርፍ እድገት የአመለካከት ለውጥን ይፈልጋል። የአገር ምርትን የመጠቀም ባህልን የማዳበር ጥረት ለዘርፉ እድገት ቀላል የማይባል ሚና አለው። በዚህ ረገድ አቶ ሰለሞን «ብዙዎቻችን ስለማናውቃቸው እንጂ የሌሎች አገራት ብራንድ ተለጥፎባቸው ከትልልቅ መሸጫዎች የምንገዛቸው ጫማዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የተመረቱ ናቸው። የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። ሕዝባችን የአገሩን ምርት የመጠቀም ባህል እንዲያዳብር ማድረግ ይገባል። ለዚህም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት መከናወን አለባቸው» ይላሉ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# እንደማመጥ

**ሙሉቀን ታደገ**

ለብዙ ወራት ተሰውሮ የነበረው ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል ተነስቶ በሰፈራችን ከሚገኘው ዋርካ ስር ቆሞ ይጮሃል። ሰዓቱ የሰፈራችን ሰዎች ወደ «በተስኪያን» የሚሄዱበት ነው። በእኛ ሰፈር ያሉ ሰዎች በሙሉ በተስኪያን ሳይሄዱ አስቀድመው ምንም አይነት ስራ አይጀምሩም። ዛሬ ግን ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ከብዙ የአርምሞ ቀናት በኋላ መጮህ ስለጀመረ በሰፈራችን የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በተስኪያን የሚገኘውን ቡራኬ ትተው የይልቃ አዲሴን ንግግር ለማዳመጥ ተቻኩለው ወደ ዋርካው ስር ተሰባሰቡ። ሰዎች በመሰባሰብ ላይ እያሉ ይልቃል አዲሴም...

**አስበን እንስራ ስነገም እንዲሆን፣**
**ይሁን ይሁን ብለን የማይሆን እንዳይሆን።**

« አለ አንዳርጌ መስፍን » እያለ ደጋግሞ ያምቧርቅ ነበር።

የሰፈራችን ሰዎች ወደ ዋርካው ተሰባስበው ቦታቸውን መያዛቸውን ከተመለከተ በኋላ ይልቃል አዲሴ ራሱን ለንግግር እያዘጋጀ እህ ..እህ... ብሎ ጉሮሮውን ጠራረገ። ንግግሩንም እንዲህ ሲል ጀመረ ......አሁን አሁን በሰፈራችንም ሆነ በእድራችን በሰፊው እየተንሰራፋ የመጣ እና የእድራችንን ህልውና ሊያጠፋ የተቃረበ ከፉ ወረርሽኝ ተከስቷል። ይህ ወረርሽኝ አለመደማመጥ ነው ! በኃይማኖት አለመደማመጥ፣ በፖለቲካ አለመደማመጥ፣ በእድር እና በሌሎች ሁነቶች አለመደማመጥ።

የሰፈራችን እና እድራችን ነዋሪዎች፣ መሪዎች እንዲሁም የተፎካካሪ ኃይሎች በመደማመጥ እና በመነጋገር ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ ሁሉን ነገር በግብታዊነት እና በትዕቢት ለማስፈጸም ሲፋተጉ ይስተዋላሉ። ይህ ፈጽሞ ልክ አይደለም።

እንደእኛ ሰፈር እና እድር ተሞክሮ ከዚህ ቀደም በሰፈራችን እና በእድራችን ተከስተው ከነበሩ አያሌ ችግሮች መካከል አንዳቸውም በጉልበት ሲፈቱ አላየናቸውም። ኢጋጥመውን የነበሩ ችግሮቻችንን በጉልበት ለመፍታት በሄድንባቸው ዘመናት ሰፈራችን እና እድራችን እጅግ አስቻጋሪ የሆነ ሁለተናዊ ቀውስ ገጥሟቸው እንደነበር ታሪክ ፍንተው አድርጎ ያሳየናል። በነገራችን ላይ የዓለም ተሞክሮም የሚየሳየው ይህንኑ ሃቅ ነው።

የዓለም ታሪክ በግልጽ እንደሚያሳየን በአንድ አገር ላይ ችግር በተፈጠረ ወቅት የተፈጠረውን ችግር በውይይት እና በጥበብ የፈቱ መሪዎች እና ተፎካካሪዎች እንዲሁም ህዝቦች በትልቁ አትርፈዋል። በአንጻሩ ግብዝ የሆኑ መሪዎች እና ተፎካካሪዎች እንዲሁም ህዝቦች የተፈጠሩ ችግሮችን ሁሉ በጉልበት ለመፍታት ሄደው ያጋጠማቸው ኪሳራ የሚታወቅ ነው።

ሰዎች ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት ሁለንተናዊ መስተጋብር ሰው ናቸውና በመካከላቸው የፍላጎቶች አለመጣጣም ይከሰታል። እነኝህ የፍላጎቶች አለመጣጣም በግብተኝነት ለመፍታት የሞከሩ ኃይላት በሚፈጥሩት ፍትጊያ የሰውን ህይወት ከመቅጠፍ ውጭ አንድም ቀን መፍትሔ ሲያመጡ አላየናቸውም። የአንደኛው እና የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተመልከቱ ፤ መሪዎች እና ፖለቲከኞች በነበራቸው መስተጋብር የፍላጎቶች አለመጣጣም ተከሰተ። የተከሰተውን ችግር በውይይት ከመፍታት ይልቅ ልባቸውን ከግመል ሻኛ በላይ አሳብጠው «ይዋጣልን» አሉ። አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ጦር ሰበቁ ። ዘግናኝ ጦርነቶችን አካሄዱ። በጦርነቱ ህዝባቸውን አስፈጁ።

ሶቅራጥስ «ቁጣ የሚያሸነፍህ እንደሆነ ክፋት ቅን ሃሳብህን ለውጦ የራሱ ተከታይ እና ተገዢ ትሆን ዘንድ ማርኮሃልና ራስህን ከሰው ወገን አትቁጠረው። » ይላል። እውነት ነው፤ ቀና ሀሳብን ማፍለቅ ካልቻልን እና የሚፈጠሩ ችግሮችን በመስማማትና በውይይት መፍታት የማንችል ከሆነ ራሳችንን እንደ ሰው መቁጠር አይገባንም። በእኛ ሰፈር ያሉ ሰዎች፣ የዕድር መሪዎች እና ተፎካካሪዎች ከሶቅራጥስ ሀሳብ ተነስተን ብንገመግማቸው ሰዎች ናቸው ለማለት እንቸገራለን።

በሰፈራችን እና በእድራችን የሚከሰቱ ማናቸውም አይነት ችግሮችን የውጭ ሰው ሳይሰማ በጓዳችን ተወያይተን ከመፍታት ይልቅ ይዋጣልን ማለትን ስንመርጥ ይስተዋላል። በተለይ እድር እና ሰፈራችንን የምትመሩ እንዲሁም ለመምራት የምትፎካከሩ ኃይሎች እኛን ለመምራት ከፈለጋችሁ በመጀመሪያ ደረጃ የመሪዎች «ሀሁ» የሆነውን ራስን መግዛት እና መቆጣጠር ተለማመዱ። ራስን መግዛት እና መቆጣጠር የሚችል ሰው የሚፈጠሩ ችግሮችን በንግግር እና በውይይት ለመፍታት አያዳግተውምና። ራስን መግዛት እና መቆጣጠር መቻል በግብዞች የሚፈጠሩ የጥፋት ሰደድ እሳቶችን የሚያጠፋ ሁነኛ መድኃኒት ነው።

ነገር ግን ራስህን ከፍተኛ ሰገነት ላይ በማስቀመጥ የሰዎችን ሀሳብ እና መብት በመደፍጠጥ በአንድ ማህበረሰብ የሚፈጠሩ ችግሮችን በጉልበት ለመፍታት መጣር ትርፉ ውርደት ነው። የበርካታ አገራት ታሪክ የሚያሳየን ይህንኑ ሀቅ ነው።

እደግመዋለሁ ! አሁን ላይ በሰፈራችን እና በእድራችን እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በጥበብ፣ በመነጋገር እንዲሁም በመወያየት ከመፍታት ይልቅ በግብታዊነት እና በጉልበት ለመፍታት ሲሞከር ይታያል። ልማትን ለተጠማ ሰፈር እና እድር መገፋፋት እና መገዳደልን መምረጥ፤ በጠራራ ፀሐይ የመንገድ ላይ መብራት የማብራት ያህል እርባና የሌለው ተግባር ነው።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ይህን ንግግር እያደረገ እያለ ሁሉም የሰፈራችን ሰዎች ጸጥ እረጭ ብለው እያዳመጡ ነበር። ነገር ግን ሁሌም ሳይፈቀድለት የሚናገረው አብሿሙ ክንፈ ጉደታ በይልቃል አዲሴ ንግግር ላይ ተደርቦ የይልቃል አዲሴን ንግግር አቋረጠው።

ባለፈው እንደነገርኳችሁ የሰፈራችን ሰዎች ክንፈ ጉደታን አብሿም ይበሉት እንጂ ክንፈ ጉደታ የእውነት አብሾ መጠጣቱን በእርግጠኝነት መናገር የሚችል ሰው የለም።

የይልቃል አዲሴን ንግግር የአቋረጠው አብሿሙ ክንፈ ጉደታ «ይልቃል አዲሴ ያደረጋቸው ንግግሮች በሙሉ እውነታ አላቸው። እኔም ከሱ ሃሳብ ላይ የምጨምረው አለኝ» አለና ንግግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ ....

እርስ በርስ የማይስማማ ህዝብ ለውጭ ጠላት አመቺ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። የእኛ ሰፈር እና እድር ደግሞ በርካታ የውጭ ጠላቶች አድፍጠው የሚመለከቱት መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ይህ እየታወቀ ስለምን በመነጋገር እና በውይይት ችግሮቻችን መፍታት ተሳነን ? ፈላስፎች እንዲህ ይላሉ፤ ብልህ እና አስተዋይ ሰው ለዘመኑ የሚስማማውን ነገር ያውቃል። ስለራሱም ያስተውላል። አንደበቱ ክፉ ከመናገር ይቆጠባል። እኛ ግን ብልሃት ጎድሎን ለዘመኑ የማይመጥን እና ወቅቱ ከሚፈልጋቸው አስተሳሰቦች ጋር የተጣረሱ አካሄዶችን እየመረጥን ነው። ከዚህ አንጻር የእኛ ሰፈር ሰዎች፣ መሪዎች እና ተፎካካሪዎች የት ላይ ነን ? ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ።

በዓሉ ግርማ በጉልህ በሚታወቅበት መጽሐፉ በኦሮማይ እንዲህ ይላል ....«የአሮጌው ሙጣጭ የአዲሱ ትውልድ የበኩር ልጅ ነው። » እውነቱን ነው ! በ1950ዎቹ እና 60ዎቹ በውጭ አገር እና በእኛ ሰፈር መካነ -አእምሮ የተማሩ ሰዎች የእነ ማርክስ እና ሌኒንን የፖለቲካ ንድፈ ሐሳብ ጭልጥ አድርገው ጠጥተው እና ተግተው ግራ ዘመም ሳይሆኑ «ግራ ዘመም » ሆነው የበርካታ ሰዎችን ህይወት አስነጠቁን። የእነሱ ርዝራዥ እና ሙጣጭ ደግሞ የአሁኑ የሰፈራችን የበሕር /በኩር/ ልጅ ሆነው እየበጠበጡን ነው። ሁሉ ነገራችንን የቁም ሲኦል እያደረጉብን ነው።

ፈረንጆች እንዲህ ይላሉ... የሰው ሁሉ ወዳጅ የአንድ ሰው ወዳጅ እንኳን መሆን አይችልም። እውነታቸውን ነው ! የ1950ዎቹ እና 60ዎቹ ሙጣጭ ዘውጌ ማርክሲስቶች፤ የአሁኑ ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበኩር ልጆች አንድ እና መተኪያ የሌለውን ወንድማቸውን እየገፉ፤ የእድራችን እና የሰፈራችን ታሪካዊ ጠላት ከሆኑ ኃይሎች ጋር በጊዜያዊ ጥቅም ተደልልው ሳንባችንን ኢጋጥመን በአንድ አንፍንጫ እንተንፍስ ሲሉ ይስተዋላሉ። ይሁን እንጂ በጊዜያዊ ጥቅም የተገዛ ጓደኛ ችግር በገጠመህ ጊዜ አብሮህ እንደማይቆም እሙን ነው።

ጠቢባን እንደሚሉት፤ ጊዜ አግኝቶ ሳለ አለሁልህ ማለትን ለማያውቅ ጊዜው ሲያልፍበት አለሁልህ የሚለው አይገኝም። ይህ አባበል 1950ዎቹ እና 60ዎቹ ሙጣጭ ዘውጌ ማርክሲስቶች የተባለ ይመስለኛል። ልማት ለተጠማው እድራችን እና ሰፈራችን በተማሩት ሙያ እና ስልጣን አሁኑኑ መድረስ ካልቻሉ እነሱ እክል በገጠማቸው ጊዜ አብሯቸው የሚቆም ይጠፋል። ህይወት በጋሬጣ የተሞላችና አንድ ቀን እነሱን የህይወት ጋሬጣ ማጋጠሙ አይቀርም። ያኔ አንድ ሰው እንኳን አብሯቸው አይቆምም። ለዚህ መድሃኒቱ አሁኑኑ ለሁለንተናዊ ጥቅም በጋራ በመቆም እና በመደማመጥ የሚያገጥሙ ችሮችን መፍታት ብቻ እና ብቸኛው አማራጭ ነው።

የ1950ዎቹ እና 60ዎቹ ዘውጌ ማርክሲስቶችን ስመለከት «ለውሃቤ ዝናም ማየ ክልእዎ፤ ለዝናብ ጌታ ውሃ ነሱት» የሚለው የሊቃውንት ንግግርን ያስታውሰኛል። የምስራቁ ኮከብ የ1950ዎቹ እና 60ዎቹ ልጆቿን ለነገ ችግሬ ይደርሱልኛል ብላ ዛሬ ላይ የምትባለው ሳይኖራት ከሀብታም ልጆች እኩል አስተማረቻቸው። ነገር ግን «ዝናብ ለሰጠ ጌታ ውሃ ነሱት» እንዳሉት ሊቃውንት ሳይኖራት ያስታማረቻቸውን እናታቸውን መርዳት ባይችሉ እንኳን እንደነሱ ተሞላቀው ያልተማሩ ልጆቿን በዘውግ አቧድነው ባያባሏቸው ጥሩ ነበር።

ፈላስፋዎቹ እንደሚሉት፤ ሰዎችን ፍጹም ጥሩ ሊያስብሉ የሚችሉ አራት ባህሪያት አሉ። እነሱም ማስተዋል፣ መስጠት፣ መልካም ጠባይ እና ምኞትና ፍላጎትን ማሸነፍ ናቸው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባ ነገር አለ። በእነኝህ ፍጹም ሊያስብሉ በሚችሉ አራት ባህሪያት ውስጥ ቅንነት እና ችግሮች ሲያጋጥሙ በውይይት መፍታትን በውስጣቸው የያዙትን እናገኛለን። እዚህ ላይ የእኛ ሰፈር እና እድር መሪዎች እና ተፎካካሪዎች የት ላይ ናቸው ብሎ መጠየቁ ተገቢ ይመስለኛል።

በነገራችን ላይ በውይይት የማያምኑ ሰዎች በትንሽ ድል ራሳቸውን የሚኮፍሱ ግብዞች፣ አብዝተው የሚቸኩሉ እና ማስተዋል የተሳናቸው ናቸው። ፈላስፎችም ለተስፋ ፈተናው እና እንቅፋቱ መቸኮል ነው ይላሉ። ጠንቃቆች እና በውይይት የሚያምኑ ሰዎች ማንኛውንም ውሳኔ ሲወስኑ አይቸኩሉም። ምክንያቱም የነገ ተስፋቸው እንዲበላሽ አይፈልጉምና።

«በነገራችን ላይ በውይይት የማያምኑ ግብዞች ውይይትን በዋናነት የሚጠሉበት እና ጦርነትን እንደ አማራጭ የሚጠቀሙት ቀናተኛ ስለሆኑ እና አማራጭ የምፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ ስለማይችሉ ነው። ለዚያም ነው ፈላስፎች ልጇ ከቅናት ተጠበቅ፤ ተጠንቀቅ ቅናት የመለያየት በር ናትና ብለው የሚያስተምሩት ።»ብሎ ወደ መቀመጫው ተመለሰ።

አብሿሙ ክንፈ ጉደታ ንግግሩን ሲጨርስ ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ከአቆመበት ቀጠለ ....

ለመፍትሔ የሚደረጉ ንግግሮች እና ውይይቶች ከአሽሙር የጸዱ እና ቀጥተኛ መሆን አለባቸው። በውይይት መካከል አሽሙር ወይም ሽሙጥን መጠቀም ወደአልተፈለገ አቅጣጫ ይወስደናል። ይህንን በምሳሌ ላሳያችሁ አንድ እግሩ ላይ የተፈጥሮ ጉዳት ያለበት፤ መራመድ የማይችል እና በመቀመጫው እየተንኳተተ የሚሄድ ሰው ነብር። አንድ ቀን ልብስ ለማሰፋት ወደ ልብስ ሰፊዎች ሱቅ አቀና። ለኮት የሚሆን ልብስም አስቀደደ። ልብስ ሰፊው መራመድ ለማይችለው ሰው በቀነ ቀጠሮ ኮት ሰፍቶ እንደሚጠብቀው ነግሮት ተሰነባበቱ። ልብስ ያስቀደደው እና መራመድ የማይችለው ሰውየም በተቀጠረበት ቀን ሂዶ የተሰፋውን ልብስ ለሙከራ አጠለቀ። ልብስ ሰፊውም የሰፋትን ኮት ያደነቀ አስመስሎ በአሽሙር ወይ ኮቲት! ወይ ኮቲት! እያለ ተሳለቀ። ልብስ ያሰፋውን ሰውየ በእግርህ መራመድ የማትችል ኮታታ ነህ በማለት ሰደበው። ቅኔው የገባው ሰውየም ከልብስ ሰፊው ጋር የነበረው መልካም ግንኙነት ተቋጨ። ሊቃውንት «ህይወት ወሞት ውስተ እደ ልሳን፤ ህይወትም ሞትም በአፍ ይመጣሉ። » ማለታቸው ለዚህ አይደል?

ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ቀጥሎ... የእኛ ሰፈር ሰዎችን፣ ንቃተ ህሊና እና ውስጠ ህሊና ምን በላው ? ሲል ጠየቀ። ይህ በእንዲህ እንዳለ አብሿሙ ክንፈ ጉደታ ንቃተ ህሊና እና ውስጠ ህሊና ልዩነቱ ምንድን ነው? ሲል ጠየቀ።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ የተጠየቀውን ሲያብራራ፤ ንቃተ ህሊና ማለት የማሰብ ችሎታ ነው። ነገሮችን መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል። ውስጠ ህሊና ግን የሚሰጠውን መቀበል ብቻ ነው። ውስጠ ህሊና እንደ መረጃ ማዕከል ነው።

አሸናፊ ሆነን መውጣት እንድንችል እና ሁልጊዜም በታሪክ በጥሩ ተምሳሌትነት ለመጠቀስ ከተፈለገ ንቃተ ህሊናችንን አወንታዊ ልምዶችን እንዲያዳብር እናለማምደው። ንቃተ ህሊናችን አወንታዊ ልማዶችን ማዳበር ከቻለ ደግሞ ውስጠ ህሊናችን በጎ ነገሮችን ስለሚያስቀምጥ ክፉ ተግባራትን ከመፈጸም እንታቀባለን። በነገራችን ላይ ሰዎች ፍላጎቱ ካላቸው አወንታዊ ልምዶችን በየትኛውም እድሜ ላይ መጀመር ይችላሉ። ለእዚህ አባባል በርካታ ማሳያዎች ቢኖሩም ካለን ጊዜ አንጻር አንዱን ብቻ ነጥለን እንመለከት። ለምሳሌ አንድ ሰው በወጣትነት ዘመኑ ለንቃተ ህሊናው መጥፎ ነገሮችን እየነገረ እና እየመገበ በርካታ ወንጀሎችን ሊፈጽም ይችላል። ነገር ግን እድሜው ሲገፋ እና ቆርቦ ሲመነኩስ ግን ንቃተ ህሊና በበጎ ነገር ስለሚሞላ፤ በጎ ነገሮችን እያደረገ ለአእምሮው እና ለፈጣሪው ለመገዛት ሲጥር እንመለከታለን።

ስለሆነም ንቃተ ህሊናችንን በበጎ አስተሳሰቦች ሞልተን በጎ ተግባራትን ለማድረግ በየትኛውም የእድሜ ዘመናችን ላይ መጀመር እንደሚቻል ሁሉም ሰው ሊገነዘብ ይገባል። በማንኛውም ሁኔታ ችግሮችን በኃይል ከመፍታት ይልቅ በቅንነት ለመወያየት ቅድሚያ እንስጥ።

በመጨረሻ «ሐንካስ በአግረ ዕውር ሖረ፤ ዕውርኒ በዐይነ ሐንካስ ነጸረ ወበክልዔሆሙ ወይንየ ተመዝበረ .... አንካሳ በእውሩ እግረ ሄደ፤ እውሩ በአንካሰው ዐይን አየ » እንዳሉት ሊቃውን በሰፈራችን እና በእድራችን የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ ወደሚፈለገው የእድገት ጎዳና ለመግባት ዐይን ያለው እግር ይሸከም፤ እግር የሌለውም ዐይን ከሌለው ትከሻ ላይ ተቀምጦ ዐይን የሌለውን ይምራ። እንደዚህ ተደጋግፍን መኖር ይጠበቅብናል። ለዚህ ሁሉ ግን መደማመጥ መቅደም አለበት ብሎ ንግሩን ሲጨርስ የሰፈራችን ሰዎች በጭብጨባ አጀቡት። ስብሰባውም በዚሁ ተቋጨ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ረመዳንን በመንዙማ

መልካምሥራ አፈወርቅ



## ኢድ ሙባረክ

የኢትዮጵያ ታሪክና መንዙማ የሚጀምረው ቁርአን መቀራት ከያዘበት ዘመን አንስቶ መሆኑ ይነገራል። ነብዩ መሐመድና የኢትዮጵያውያን ታሪክ መሠረት በውል የተጋመደ ነው። ቢላልን ጨምሮ፣‹‹ሱሀባዎች›› የተሰኙ የነብዩ ረዳቶች፣ ሞግዚታቸው እሙ አይመንና የሌሎች በርካቶች ማንነት ከኢትዮጵያ የዘር ሐረግ ይመዘዛል።

አበሾቹ ነብዩ መሐመድን ከመውደዳቸው የተነሳ በዜማና ግጥም ያወድሷቸው፣ ያመሰግኗቸው ነበር። በወቅቱ ይህን ያወቁት ነብዩ መሐመድ በፈቃዳቸው ይሁንታ እንደሰጧቸውም ታሪክ ይነግረናል።

መንዙማ የዓረብኛ ቃል ነው። ትርጓሜውም ገጠመ፣ አደራጀ፣ ደረደረ የሚል ፍቺን ይሰጣል። ቃላትና ሐረጎችን፣ ስንኞችና ግጥሞችን በትክክለኛ አሰናነድ ማስቀመጥም መንዙማን ይገልጸዋል። መንዙማ የእስልምና ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ የሚጻፍ በመሆኑ በባሕርይው ከሌሎች ግጥሞች ይለያል። መንዙማ ጥንታዊ የሚባል ታሪክ አለው። ለኢድ በዓልና ለታላቁ የረመዳን ወር ለምስጋናና ውዳሴ ይውላል።

መንዙማ በሀገራችን በተለይ በወሎና አሮሞ ሕዝቦች ዘንድ መለመድ የጀመረው ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት ነበር። በሰሜንና ማዕከላዊ አቅጣጫም በወሎ ሙጃሂድ በስፋት ይዘወተር ነበር። የሶማሌና የሐረር መንዙማም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው።

የወቅቱ ዜማና ግጥሞችም ትክክለኛውን የኢትዮጵያዊነት ቀለም የተላበሱ ስለመሆናቸው ጥናት ያካሄዱ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ብዙዎች እንደሚሉትም መንዙማ፣ እስልምናንና ነብዩ መሐመድን ነጣጥሎ ማየት አይቻልም። ሁሉም በአንድ ድር በተዋቀረ ጥብቅ ገመድ ይተሳሰራሉ።

የመንዙማ ግጥሞች ባብዛኛው ፈጣሪን የሚያመሰግኑ ፣የነብዩ መሐመድን ክብር የሚያወድሱ ናቸው። ይህ እውነታም ዜማው ለዓመታት ጆሮ ገብ ሆኖ ከልብ እንዲወደድ አስችሏል።

ሰዎች የፈጣሪን ጥበብ ማድነቅና ማወደስ ሲፈልጉ ፣ነብዩ መሐመድን ማክበር ማወደስ ሲሹ የእንጉርጉሮ ዜማን ይጠቀማሉ። የመንዙማ ግጥሞች በሚደመጡ ፣ ጊዜም ማንኛውም ፣ ሰው በዋዛ ፣የሚጽፋቸው፣ ስንኞች እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ይቻላል። ይዘቶቹ ጥልቀት ያላቸውና በእጅጉ አመራማሪ የሚባሉ ናቸው።

ሼህ አሕመድ ሼህ ሲራጅ የተባሉ የወሎ ሰው የታወቁ ገጣሚ እንደሆኑ ይነገራል። እኚህ ሰው ግጥሞቻቸውን የሚያዘጋጁት በዓረብኛ ሲሆን በኦሮምኛ ቋንቋም ይገጥማሉ። ሼህ አሕመድ ፈጣሪን ለማወደስ የሚጠቀሙበት ቃል በእጅጉ የረቀቀና ለነብዩ መሐመድ የሚሰጡት ምሳሌም ከሌሎች የተለየ ነው ።

እንደ አጥኚዎች ግምት በመንዙማ ግጥሞች ውስጥ የሚስተዋሉትን ፍልስፍናዎች ባብዛኛው ትውልዱ የደረሰባቸው አይደለም። ብዙዎች እንደሚሉትም ግጥሞቹን መርምሮ በወጉ ለመረዳት ጥሩ አንባቢና ብቁ ተመራማሪ መሆን ያስፈልጋል ።

የመንዙማ ግጥሞች የተለየ ማራኪነት አላቸው። የፈጣሪን ኃያልነትና የነብዩ መሐመድን መወደድ ለማሳየት በተለየ ቃል ይገለጻሉ። ነብዩ በሚታወሱበት በዚህ የረመዳን ወር ታዲያ ቁርአን በማንበብና ታሪካቸውን በማንሳት ለፈጣሪ ያላቸውን ክብር በመንዙማ መግለጽ የተለመደ ነው። በታላቁ የረመዳን ወር በመንዙማ ፣ በእንጉርጉሮና ምክር፣እንዲሁም በነሺዳ ውስጠት ይገለጻል።

መንዙማ ከሁሉ አስቀድሞ እስልምና ሲታወጅ አንስቶ የተዋቀረ መሠረት አለው። በግብጽ፣ ፓኪስታንና፣ ቱርክም ይታወቃል። በነዚህ ሀገራት ትልቅ ዕውቅና የተቸራቸው ገጣሚያን ተሳትፎ አርፎበታል። ሁሉም በሚባል መልኩ ትኩረታቸው የሚገለጸው የነብዩ መሐመድን ታሪክና ማንንነት ዕውቅና በመስጠት ነው።

በሀገራችን የመንዙማ ጥበብ በተለየ መልኩ ይቀረጻል። መንዙማዎችን በማዘጋጀት፣ ግጥምና ዜማውን በመንደፍ፣ የነብዩን ማንነት ለዓለም በማስተዋወቅ ላይ ያተኩራል። የነብዩ መሐመድን የሕይወት ታሪክ መሠረት በማድረግም መልዕክታቸው ፣ ውጣወረድና ትግላቸው ሁሉ በመንዙማው ይንጸባረቃል።

ከገጠር እስከ ከተማ ያሉ የእስልምና ዕምነት ተከታዮች የነብዩ መሐመድን ገድል ለማውራት የሚያህላቸው የለም። ደግነታቸውን፣ ታላቅነታቸውን፣ የሚገልጹበት አንዱ መንገድ የመንዙማ ጥበብ ነው። መንዙማ የእስልምና ዕምነትን ዕውቀት ለማስጨበጥ ጭምር ያገለግላል።

ኢትዮጵያ የእስልምና ሀይማኖትን ተቀብላ ያስፋፋች ሀገር ነች። በሀበሻው ንጉስ ነጃሺ ዘመን ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ ፍትሕና ሐቅ የማይጓደልባት፣ ምድር መሆኗን ለተከታዮቻቸው በገለጹት መሠረት መጀመሪያ አስራ ሁለት ወንዶችና አራት ሴቶች በእንግድነት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን ታሪክ ይነግረናል።

በዚህች ምድር የነበረው ሰላምና መልካምነት እንደተባለው በመሆኑም ውሎ አድሮ ሌሎች አማኞች ወደ አገረ ኢትዮጵያ ተጓዙ። እስልምና ያለአንዳች ችግር ተስፋፍቶም የዕምነቱን ተከታዮች በብዙ ቁጥሮች ተበራከቱ።

ኢትዮጵያ ከሌሎች የእስልምና ተከታይ ሀገራት ዕምነቱን በመቀበል ቀዳሚውን ትይዛለች። ይህ ቀደምትነትም ከነብዩ መሐመድ ጋር የጠበቀ ቅርበት እንዲኖር አስችሏል። ይህ ጥብቅ ቁርኝት የፈጠረው ጽኑ ፍቅርም በመንዙማ ጥበብ የሚገለጽ ሆኗል።

በሀገራችን የእስልምና ዕምነት ተከታዮች መንዙማን በአማርኛና በዓረብኛ በማዜም ለምስጋና ይጠቀሙበታል። ከጥንት ጀምሮ አብዛኛው የእምነቱ ተከታይ ሕይወትና ኑሮ በገጠር ስለነበረም አማኙ ስለእምነቱ በቂ ዕውቀት እንዲኖረወና ፣ከሃይማኖት ሥርዓት ጋር እንዲገናኝ በመንዙማ መልዕክት ማስተላለፍ መቻሉ ይነገራል ።

ሰለእስልምና በቂ ዕውቀት ያላቸው ዑላማዎች ሙስሊሙን በዕውቀት ለመድረስ ሲሉ መንዙማን እንደቀኝ እጅ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። በዚህም ቁርዓንና ትርጉሙ፣ ሀዲስና የዓረብኛ ቋንቋ ጭምር ሲስፋፋ ኖሯል። ከሁሉም ደግሞ የነብዩ መሐመድ ታሪክና ማንነትን በማስተዋወቅ መንዙማ ያበረከተው አስተዋፅዖ ጎልቶ ይገለጻል።

መንዙማንና ስንኙን ለማዘጋጀት በጥበቡ የተካነ፣ በስጦታው የታደለ ሰው ያስፈልጋል። መንዙማ በማንኛውም ሰው አንደበት በግምት አይዘጋጅም። ቁርዓንን ማወቅ ሀዲስን መረዳት፣ ስለነብዩ ጥንተ ታሪክ በወጉ መመራመር ግድ ይላል። የዓረብኛ ቋንቋን መናገር፣ መስማትና መጻፍም ለጥበቡ እድገት በእጅጉ ያግዛል።

አማኞች እንደሚሉት ደግሞ በወሎ ምድር እስልምና በሰፋበት ማዕከል የምትገኘው ‹‹አዛሩል አበሻ›› የጠቢባኑ ዑላማዎች መገኛ ናት። በዚህች አካባቢ በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን በሁለት አውራጃዎች ብቻ ከስድስት መቶ በላይ ሊቃውንት ተፈርተዋል።

ከነዚህ ሊቃውንት መካከል መንዙማን በመቅረጽ የሚታወቁ ከወረባቦ እነ ሼህ ጫሌ ፣ ሰይድ ኢብራሂም ፣ ዳንኤል አወል ፣ አንይና ሌሎችም ይጠቀሳሉ። ከነሱም ቀጥሎ እነሼሕ ሲራጅ፣ ሼሕ አሕመዲን፣ የመሳሰሉ በመንዙማ ጥበብ ከተካኑት መሐል ይነሳሉ። እነዚህ ሊቃውንት በነበሩበት ዘመን የመንዙማን ጥበብ ለትውልድ ለማስተላለፍ በዛፍ ጥላ ስር ሆነው ያስተምሩ ነበር።

በዘመኑ ከሊቃውንቱ አንደበት የፈለቁ ድንቅ የአማርኛና የዓረብኛ መንዙማዎች ለመታተምና ለመቀረጽ ዕድል አላገኙም። ያም ሆኖ በፍቅርና በክብር ከትውልድ ወደትውልድ እያለፉ ዓመታትን መዝለቅ ችለዋል ።

በገጠር የተዘጋጁት የዓረብኛ መንዙማዎች ጥበቡ ለተቀዛቀዘበት የዓረቡ ዓለም መነቃቃት ታላቅ አስተዋፅዖ አበርክተዋል። መረጃዎች እንደሚጠቁሙትም የሀገራችን የዓረብኛ መንዙማዎች ታሪክንና ሃይማኖትን በመደገፍ በኩል ለሀገራቱ የጀርባ አጥንት ናቸው።

ብዙዎች እንደሚስማሙት መንዙማን የእስልምና ዕምነት ተከታይ ያልሆነ ሰው ሊያዘጋጀው አይችልም ለምን ከተባለም ከዕምነቱ ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ጨምሮ የቁርዓን ዕውቀት ሊኖር ስለሚገባ ነው። መንዙማ በአብዛኛው ግጥሞቹ ከዓረብኛ የተቀላቀሉ ናቸው። በውስጣቸውም ታሪክና ሃይማኖትን ሠንቀው በወጉ ይተርካሉ።

ሁሉም መንዙማ ግጥሙ ሲዘጋጅ ዜማው ጭምር አብሮ ይቀረጻል። በተለምዶ እንደሚለየውም ሁሉም መንዙማ ተመሳሳይ የሚባል ዜማ አይኖረውም። ይህን ስልትና ዘዴ አብሮ ለማራመድም የራስ ጥበብና ዕውቀት የሚጠይቅ ነው።

ነብዩ መሐመድ ይዘው በተነሱት የእስልምና ሃይማኖት ጠንካራ ዕምነት ለማቆም ችለዋል። በዚህ ብርቱ ማንነታቸው በርካቶች እንዲከተሏቸው ምክንያት ፈጥሮ የዓረብ አገራትን ለመመሥረት ችለዋል። ፋርስ፣ታናሽዋ እስያ፣ ሰሜን አፍሪካ፣ ስፔንና ከፊል የሕንድ ግዛት፣ ፓኪስታንና አፍጋኒስታንን በሃይማኖታዊ አስተምሕሮ በማዳረስ ዕምነቱን አስፋፍተዋል።

በነዚህ ሀገራት መካከል የተፈጠረው የባሕል፣ የሃይማኖትና የማኅበራዊ መስተጋብርም የዓረብኛ ስነጽሁፍና ቋንቋ ከሃይማኖትና ፍልስፍና ጋር ተቆራኝቶ በስፋት እንዲዳረስ ምክንያት ሆኗል። ይህ አይነቱ አጋጣሚ በፈጠረው ዕድልም በርካታ ታሪኮች ተጽፈዋል፣ግጥምና ዜማዎች ተዘጋጅተው ለጆሮ ደርሰዋል። ከነዚህ መገለጫዎች መካከልም አንደኛው መንዙማ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል። ሁሌም ታዲያ የመንዙማ ግጥማ በዜማ ሲታጀብ ለነብዩ መሐመድ ክብር በመስጠት ፣ በማመስገን ፣ በማወደስ ይሆናል ።

**እንዴት ነሁ፣**
**የኔ ጌታ፣**
**እነዴት ነሁ።**
**ጦደባ ሳይ ቁጭ ብሉ፣**
**መዲና ቁጭ ብሉ፣**
**ከኋሳ ከፊቱ ፋኖስ አስከትሉ።**
**ገመሉ መጣና አሕመድን ቢያየው ፣**
**ተንበረከከና ከጫማው ሳይ ሳመው።**

በመንዙማ የሰው ልጆችን ባሕርይ ፣ የኑሮ ውጣውረድና ዕለታዊ ፈተና ሁሉ ይዳሰሳል፣ የአንዳንዶች መከፋትና ብሶት ሳይቀር ይነሳል። የመንዙማ ስንኝ ከጥንት እስከዛሬ ፈጣሪንና ነብዩ መሐመድን የሰው ልጆችን ሕይወትና ኑሮ ሲያነሳ ፣ሲያስታውስ ቆይቷል።

**አዳኚቱን ውሻ ነከሰቻት በግ፣**
**በሰው እጅ ያስ ሰው የለውም ማዕረግ።**
**ባጥፈው ደነዘዘኝ፣ ምላሴን እንደቅል፣**
**ጤናና ገንዘብ ነው የልብ የሚያናግር ።**

መንዙማ ብዙ ባይለመድም ሴቶች ጭምር ይሳተፉበታል። ለዚህ ደግሞ እማማ ዚነትንና ሌሎች ሴቶችን በምሳሌ መጥቀስ ይቻላል ። እማ ዚነት እንዲህ በማለት በመንዙማ የውስጣቸውን ተናግረዋል።

**አቤት! አቤት !አቤት ! አቤት፣**
**የጨለማው ጌታ የብርሀኑ ባልተቤት፣**
**የዘለቁ ጊዜ ሳይኛው መሥሪያ ቤት ።**
**አሜንን አለቅም የደም መሬቴ ነው፣**
**ሕመሜን የሻርኩት አሜን እያልኩ ነው።**

መንዙማ መገለጫው ብዙ ነው። በደስታ ጊዜ ውስጣዊ ስሜት ይገለጽበታል። በሠርግ ወቅትም ሙሽሮች እንዲህ ይወደሱበታል።

**ጀማሊል ዓለም፣**
**ጀማሊል ዓለም፣**
**ባየው ጊዜ አምሮ ፣**
**እንግዲህ ጀመርኩኝ ፣**
**የደስታ እንጉርጉሮ።**
**ያጣመረን አላህ- ከአንድ እናት ማህፀን፣**
**በአንድ ጎጆ አጥር- መስመለን አድገን፣**
**የልቤ ደስታ - እጅጉን አፈነው።**
**አሉሀም ዱህሊላሂ፣**
**አይኑን ባይኑ ሳየው፣**
**ጀማሊል ዓለም፣**
**ጀማሊል ዓለም፣**
**እንግዲህ ተቀበል - የፍቅር አዝማሪ፣**
**ታጥቄያለሁ መውደድ- ታጥቄያለሁ ሱሪ።**
**በረካ እንዲንቧቧ- ሐሴት እንዲሞላ፣**
**እንበል ነብይ፣ ነብይ- እንበል ሰለላ ።**

መንዙማ በተለየ ዜማ ታጅቦ በውብ ቅላጼ ተውቦ ለጆሮ ሲደርስ በእጅጉ ይማርካል። መንዙማን አስተውሎ ላደመጠው ከማራኪ ድምፀቱ ባለፈ ትርጉም ያለው መልዕክት ማስተላለፉ አይቀሬ ነው። አንዳንዴ ደግሞ መንዙማን የወደዱ፣ ምስጋና ማድረስን የለመዱ መልሰው ለመንዙማ ውዳሴን ያሰማሉ እንዲህ በማለት ።

**በአሪፍ ሆጅ ሁሴን ሳይ ተጠምጥማ**
**በእሷ እያዜሙ ስንቱ ሰው ደማ**
**ልቤን ወሰደች እቺ መንዙማ**

መንዙማ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ በጾም ጸሎት ፣ በስግደት በሚቆይበት በታላቁ የረመዳን ጾም ወቅቱን እየዘከረ ፣ ምስጋና የሚቀርብበት ጥበብ ነው።መንዙማና ረመዳን ተደጋግፈው፣ በአንድ ተጣምረው በሚደምቁበት በዚህ ጊዜ በግጥሞቹ የሚተላለፉ መልዕክቶች ትርጓሜቸው በተግባር ይገለጻል። መረዳዳት፣ መተዛዘን፣ እንዲሰፍን፣ መስጠት በረከት ሆኖ እንዲዘልቅ አስተዋፅዖው ይጎላል።

ለመላው የእስልምና ዕምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለአንድ ሺህ144 ኛው የዒድ አልፈጥር በአዓል በሰላም አደረሳችሁ እንላለን ። ‹‹**ኢድ ሙባረክ**››

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## በትምህርት ተቋማት ዙሪያ ያሉ መዝናኛ ቤቶች ስውር ተግባር

ሰላማዊት ውቤ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና ጊቢ ዙሪያ ያሉ መዝናኛ ቤት ተጠቃሚዎች ዘንድ ግራ አጋቢ ንግግሮችን የቃል ምልልሶችን ሲለዋወጡ መስማት የተለመደ ነው። አንድ ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ የዋናው ካምፓስ ተማሪ ቤቶቹ ሻይ ቡና፤ኬክ፤ ሳንቡሳ ቦንቦሊኖ፤ሳንዱችና ምግብ የሚሸጥባቸው እንደሆኑ በይፋ ባለቤቶቻቸው ቢያስታውቁም ሴት ፈላጊ ወንዶች ከደላሎች ጋር የሚቀጣጠሩባቸው እንደሆኑ ይናገራል። ሱሱ በብርቱ የተፀናወተው አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ የዩኒቨርስቲ ተማሪ የገዛ ሴት ጓደኛውን ለነዚህ ደላሎች አሳልፎ እስከመስጠት የሚደርስ አሳፋሪ ተግባር እንደሚከውንም ይነገራል። አንዳንድ ወንዶች ልጃገረድ እንዲሁም ቆንጆና ላቅ ያለ ዕውቀት ያላት ሴት ተማሪ ለማጥመድ ወደዚሁ ስፍራ ጎራ ይላሉ። አደንዛዥ ዕጾችን የሚያዘዋውሩ ወንዶች በርካታ መሆናቸው ይነገራል።

የዩኒቨርስቲውን ዋና ጊቢ የውጭ አጥር ግራና ቀኝ ይዘው እስከ እቴጌ መነን የልጃገረዶች ትምህርት ቤት አጥር ሥር የተወጠሩት የላስቲክ ቤቶችና የቆሙት ኪዎስኮች በአብዛኛው ዋና ከሚሉት ተግባራቸው በስተጀርባ ሥራቸው እንደዚህ ዓይነት ዕፆችን ማቀባበል መሆኑም በስፋት ይነገራል። በነዚህ ቤቶች ቢራና ካቲካላ(የሀበሻ አረቄ) ይሸጣል። እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓትና ከዚያ በላይም አገልግሎት ይሰጣሉ። አብዛኞቹ ተጠቃሚዎችም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ናቸው።

ሰሞኑን ስካይ ላይት ሆቴል ከሚያዝያ 2015 እስከ ሚያዝያ 2016 በሚዘልቅ የአንድ ዓመት የፀረ አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚነት መድረክ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት ፕሮፌሰር ሰለሞን ተፈራ ሲናገሩ፣ አደንዛዥ እፅ ከደቡብ አሜሪካ ብራዚል በኢትዮጵያ አየር መንገድ በኩል በሕገወጥ መንገድ ሲገባ በየጊዜው መያዙ በመገናኛ ብዙኃን ይሰማል።



በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአዕምሮ ትምህርት ክፍል ባልደረባና በግላቸውም የሪላሰን የአዕምሮ ሕክምና እና የሱስ ተሐድሶ ማዕከል መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ፕሮፌሰር ሰለሞን እንደሚናገሩት፣ ኮኬን የተባለው አደገኛ እፅና ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መድኃኒቶች ያለማዘዣ ለወጣቶች ይሸጣሉ። በዩኒቨርስቲው ዙሪያ ባሉና በሌሎች መቃሚያ ቤቶች አማካኝነት አሁን የኮኬን ዕፅ ተጠቃሚነት ጨምሯል።

በእንዲህ ዓይነቶቹ ቤቶች አማካኝነት በሀገራችን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በሱስ ተገዢ ሆነዋል። ለዚህ ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው። ኢትዮጵያ በዓለም ከፍተኛ የጫት አምራች አገር ናት፣ ከሚመረተው 85 በመቶ በላይ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ይውላል። ባለፉት 20 ዓመታት የቢራ ምርት በከፍተኛ መጠን ጨምሯል። እንዲሁም ከጠላና የሀበሻ አረቄ ጀምሮ በጎጆ ኢንዱስትሪ በቤት ውስጥ የሚመረቱ ባሕላዊ መጠጦችም ስርጭት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ታዳጊዎች እነዚህን የአልኮል ይዘት ያላቸውን መጠጦች መሸጥ ቢከለከልም እነዚህ በፋብሪካ የሚመረቱና በቤት ውስጥ የሚመረቱ ባሕላዊ መጠጦች በትምህርት በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዙሪያ ባሉ ቤቶች በስውርም ሆነ ሲሸጡ ይስተዋላል። በቤቶቹ በስውር ካናቢስ፤ኮኬንና ሄሮይን መሰሎቹን የተከለከሉ የአደገኛ እፅ ዝውውርም ይካሄዳል። ጫት ይቃምባቸዋል ሲጋራም ይጨስባቸዋል። በነዚህ ቤቶች ምክንያት ተማሪዎች በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ለአልኮል መጠጦችና ለአደገኛ ዕጾች ሱሰኝነት የሚጋለጡበት ሁኔታ ቀላል አይደለም። ለሱሰኝነት ከመጋለጣቸውም በላይ የትምህርታቸውንና የጤንነታቸውም ጉዳይ አደጋ ላይ ይወድቃል።

እንደ ፕሮፌሰር ሰለሞን ገለፃ፣ አደገኛ እጾችና መድኃኒቶች በዋናነት ማዕከል የሚያደርጉና የሚጎዱት የሰውነት ክፍል አንጎልን ነው። አንጎል ደግሞ የአዕምሮ መነሻ ነው። አዕምሮ የማሰብ፤ የማገናዘብ፤ ትምህርት የመቀበል፤ሥራ የመሥራት ችሎታን የሚከውን ነው። በአጠቃላይ ሕይወትን በጤናማ መስመር የመምራት ችሎታን የሚወስን ነው። በመሆኑም በአዕምሯቸው ላይ የሚከሰት ጉዳት አጠቃላይ የሕይወት ቀውስ የሚያስከትልባቸው ነው። ለአብነት ካናቢስን አዘወትረው የሚጠቀሙ ወጣቶች የአስተሳሰብ መጠን መለኪያ (የአይኪው) መጠናቸው በስምንት ከመቶ እንደሚቀንስ በጥናት ተረጋግጧል። ሀሺሽ የሚጠቀሙ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ውጤታቸው ከማይጠቀሙ ተማሪዎች በአንድ ከመቶ ያነሰ ነው። በአዕምሯቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር ከዚህም በላይ በብዙ ጥናቶች ተረጋግጧል።

ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየው ጥንቃቄ ካልተደረገና በጊዜ እርምጃ ካልተወሰደ የተጠቂዎች ቁጥር እየጨመረና እየተባባሰ ይሄዳል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት በስካይላይት በተካሄደው መድረክ ላይ የታደሙት አቶ ኤልያስ አካላይ፣ በትምህርት ተቋማት በተለይም በዩኒቨርሲቲዎች ዙሪያ ወጣቶችን ለእንዲህ ዓይነት ጉዳት የሚዳርጉ ቤቶች እንዳይኖሩ የሚደነግግ ሕግ እንዳለ ይናገራሉ። የመቋሚያ ማኅበረሰብ ድርጅት ኤክስኩቲቭ ዳይሬክተር አቶ ኤልያስ፣ የአደገኛ እፅ ተጠቃሚነት ቅድመ መከላከል ባለሙያ ሲሆኑ መቋሚያ ሱስ ሳይንስ መጽሐፍም ፀሐፊና ደራሲ በመሆናቸው ብዙ ተሞክሮ አላቸው። ወጣቶች ወደ ሱስ እንዳይገቡ ለማድረግ ቀላል ቢሆንም ከገቡ በኋላ ለማስወጣት ረጅም ጊዜ እንደሚፈጅ ይናገራሉ። በፋብሪካና ከፋብሪካ ውጪ በቤት ውስጥ የሚመረቱ የአልኮል ይዘት ያላቸውን ምርቶች መቀነስ፤በተለይም በሀገር ውስጥ ከሚመረተው ጫት ከፍተኛ መጠን ያለውን ወደ ውጭ መላክ መፍትሔ መሆኑን ይጠቁማሉ። ከባሕል ጋር ተያይዞ የሚቃምባቸውን ሁኔታዎችም ቀስ በቀስ ከባሕል እየነጠሉ ሱሱን እርቃኑን በማስቀረት መከላከል እንደሚቻልም ይመክራሉ። በትምህርት ተቋማት ዙሪያ ያሉ ለእጽና ለአልኮል መጠጥ መስፋፋት ምክንያት የሆኑ ቤቶችን ከአካባቢው ማስወገድ መፍትሔ እንደሚሆንም ይጠቁማሉ። እነዚህን ቤቶች በማፍረስ ለወጣቶቹ መፍትሔ የማምጣት እርምጃ በቅርቡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋናው ካምፓስ ተጀምሯል። አሁን ላይ በተለይ ለተማሪው ጠንቅ የነበሩትና በግራና ቀኝ አጥሩ ዙሪያ የተኮለኮሉት ቤቶች ፈርሰዋል። ይሄን ተከትሎም በየክልሉ ያሉ ዩኒቨርስቲዎችም ተሞክሮውን ያሰፋታል ተብሎ ይጠበቃል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርና የዕለቱ የክብር እንግዳ ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ ለአንድ ዓመት የሚዘልቀውን ይሄንኑ የንቅናቄ መድረክ ሲከፍቱ፣ «ሀገር የሚገነባው በወጣቶች ነው። ተስፋ የሚጣለውም እንዲሁ በወጣቶች ነው። በመሆኑም ወጣቶች ከአደጋ መጠበቅ አለባቸው። ወጣቶች ለትምህርታቸው፤ለዕውቀት፤ለክህሎት ትኩረት እንዲሰጡ መታገዝ አለባቸው» ሲሉ ተናግረዋል።

የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴታዋ ወይዘሮ ሙና አሕመድ በበኩላቸው፣ በመድረኩ ወጣቶችን እንደ ሀገር ችግር ውስጥ ከሚጥሉና ከአዘናጊ ችግሮች አንዱና ዋንኛው ወጣቶች በሱስ መጠመዳቸው መሆኑን አስታውሰዋል። ዓለም አቀፍ ችግርም እንደሆነም ጠቁመዋል። በመሆኑም ሚኒስቴሩ ለችግሮቹ ትኩረት ሰጥቶ የወጣቱ አዕምሮና አካል እንዲጠበቅ፤ እንዲሁም ውጤታማ በሆኑ ተግባራት ላይ እንዲሠማሩ እገዛ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

# ዓለም አቀፍ

## የሱዳን ጀኔራሎች ደረስንበት ያሉት የተኩስ ማቆም ስምምነት ሳይከበር ቀረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሱዳኑ ግጭት ለ24 ሰዓታት የሚዘልቅ ተኩስ የማቆም ስምምነት ተደርሷል ቢባልም ስምምነቱ ሳይከበር ቀረ።

ነዋሪዎች በካርቱምና በሌሎች ከተሞች በሀገሪቱ ጦር እና በፈጥኖ ደራሽ ልዩ ኃይሉ መካከል የሚደረግ ከፍተኛ የተኩስ ልውውጥ ድምጽ እንደሚሰማ፤ ተዋጊ የጦር ጀቶችም ዒላማዎቻቸውን እየመቱ እንደሆነ ተናግረዋል።

የተጎዱትን ወደ ጤና ተቋም ለመውሰድ፣ ለሰላማዊ ሰዎች የመተላለፊያ ኮሪዶር ለመክፈትና ለሰብዓዊነት ሲባል ለ24 ሰዓት ተኩስ አቁመናል የሚል ሃሳብ ከሁለቱ ተፋላሚዎች ተሰምቶ ነበር።

ይሁን እንጂ ከ12 ሰዓት በኋላም በካርቱም የጦር ማዘዣ ጣቢያ እና አየር ማረፊያ አቅራቢያ ግጭት እንደነበረ ተነግሯል።



ዱአ ታሪቅ የተባለች አንድ የካርቱም ነዋሪ በቤት ውስጥ አንድ እሽግ ውሃ ብቻ መቅረቱን እና የቀረውን ውሃ ለሁለት ዓመት ልጇ ብቻ ብላ ማስቀመጧን ቢቢሲ ዘግቧል።

«በጣም ብዙ ሰዎች በተባራሪ ጥይት እና በሚሳይሎች እየተመቱ በቤታቸው ውስጥ ተገድለዋል« በማለት በቤቷ ውስጥ ባለ ጠባብ ኮሪዶር የቤተሰብ አባላቱ ተሸሽገው እንደሚገኙ ተናግራለች።

በካርቱም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተጠልሎ የሚገኘው ተማሪ ደግሞ አንድ ተማሪ ተባራሪ ጥይት ከመታው በኋላ ሕይወቱ ማለፉን ገልጿል።

ተማሪው የተገደለው ለተቀሩት ተማሪዎች ምግብ ለማምጣት ከተሸሸጉበት ቦታ ከወጡ በኋላ መሆኑን የሕግ ተማሪው ሞሳብ ሸሪፍ አስተድቷል።

ይህ በዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተገደለውን ተማሪ አውጥቶ መቅበር ስላልተቻለ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ መቀበሩን ቢቢሲ ዘግቧል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ቃል አቀባይ ካርቱምን ጨምሮ በሌሎች ከተሞች የሚደረገው ውጊያ መቀጠሉን እና ተዋጊ ኃይሎች ግጭት ለማቆም ስምምነት ተገዢ የመሆን ምልክት እንዳላሳዩ ተናግረዋል።

ሁለቱ ተዋጊ ኃይሎች እንደ አየር ማረፊያ፣ ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያዎችን፣ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ እና ቤተ-መንግሥትን ለመቆጣጠር ባለፉት ቀናት ሲዋጉ ቆይተዋል።

በግጭቱ ተሳታፊዎች በጀኔራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን የሚመራው የአገሪቱ መደበኛ ጦር ሠራዊት እና በጀኔራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ የሚመራው የፈጥኖ ደራሽ ልዩ የሚሊሻ አባላት ናቸው።

እነዚህ ሁለት የጦር ጀኔራሎች በሱዳን ሥልጣን ለሲቪል አስተዳደር ለማስተላለፍ ተስማምተናል ያሉ ቢሆንም፤ ጀኔራል ዳጋሎ የሚመሩት የልዩ ኃይል አባላት ወደ አገሪቱ ጦር በሚቀላቀልበት ሁኔታ መስማማት አልቻሉም።

ሁለቱ የጦር ጀኔራሎች ወደ ውይይት ተመልሰው ልዩነቶቻቸውን በንግግር እንዲፈቱ ጥሪ እየቀረበላቸው ይገኛል።

## ፎክስ ኒውስ በስም ማጥፋት ክስ 787 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ለመክፈል ተስማማ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ፎክስ ኒውስ ዶሚኒዮን የተባለው ድምጽ መቁጠሪያ ሥርዓት የሚያስተዳድር ኩባንያ ባቀረበበት የስም ማጥፋት ክስ 787 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ለመክፈል ተስማማ።

እ.አ.አ. በ2020 ከተካሄደው የአሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ፣ ዶሚኒዮንን በተመለከተ ፎክስ ኒውስ የሠራው ዘገባ ላይ ስም የማጥፋት ክስ ተከፍቶ ነበር።

ዶሚኒዮን ክሱን ሲመሠርት ካሳ እንዲከፈለው የጠየቀው 1ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር ነበር።

በምርጫው ወቅት ለቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የተሰጡ ድምጾች ተጭበርብረዋል በሚል ፎክስ ሐሰተኛ ዘገባ በማሰራጨቱ፣ ዶሚኒዮን ንግዱ ጉዳት እንደደረሰበት ገልጿል።

የፎክስ ኒውስ ኃላፊ ሩፔት መርዶክን ጨምሮ ሌሎችም የሚድያው አመራሮች ቃላቸውን በፍርድ ቤት ሰጥተዋል።

በቅርብ ዓመታት ውስጥ ፎክስ ኒውስ ላይ ከተከፈቱ የስም ማጥፋት ክሶች ትልቁ በመሆኑ ትኩረት ስቦ ቆይቷል።

ፎክስ ገንዘብ ለመክፈል ከተስማማ በኋላ ባወጣው መግለጫው ዝርዝር መረጃ ባይሰጥም ፎክስ በፍርድ ቤት ዶሚኒዮንን በተመለከተ ሐሰተኛ መረጃ ናቸው ተብለው ከቀረቡት በተወሰኑት እንደሚስማማ ገልጿል።

የዶሚኒዮን ኃላፊ ጆን ፖሎስ እንዳሉት ስምምነቱ ከገንዘብ ክፍያ በተጨማሪ ፎክስ ውሸት መናገሩንና ተቋሙ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሱን እንዲያምን ያስገድዳል። ውሸት አሉታዊ ውጤት ያስከትላል። ከሁለት ዓመት በፊት ስለ ዶሚኒዮን የተሰራጩ ውሸቶች መላው አሜሪካን አጥለቅልቀዋል። ይህም ለሴራ ትንተና መነሻ ሆኗል። ድርጅታችንንም ጎድቷል ብለዋል።

የፎክስ ጠበቆች መጀመሪያ ላይ የተጠየቀውን የ1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር ካሳ የተጋነነ ነው ሲሉ ተቃውመዋል። ፎክስ በበኩሉ «ትልቁ ጉዳት» ብሎ የሚወስደው የንግግር ነፃነት ላይ የደረሰው ገደብ እንደሆነ ገልጿል።

ለትራምፕ የተሰጡ ድምጾች ተጭበርብረዋል የሚለው የወግ አጥባቂው ፎክስ ዘገባ ሐሰተኛ መሆኑን ዶሚኒዮን ሲነቅፍ ቆይቷል።

የሕግ ቡድኖች ባደረጉት ምርመራ መሠረት የፎክስ አመራሮች እና ጋዜጠኞች የ2020ው ምርጫው ተጭበርብሯል ብለው ባያምኑም ዘገባዎቻቸው ይህንን የሚያንጸባርቁ ነበሩ።

የፎክስ ኃላፊ መርዶክ ስለ ዶሚኒዮን በፎክስ የተላለፉ ዘገባዎችን «በጣም ጤናማ ያልሆኑ» ሲሉ ቢገልጿቸውም ምንም እርምጃ አልወሰዱም።

የገንዘብ ክፍያ ስምምነት ላይ ከመድረሳቸው በፊት ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ስለ ዶሚኒዮን የተላለፉት ዘገባዎች ሐሰተኛ ይዘት እንዳላቸው ማረጋገጫ ተገኝቷል።

ዶሚኒዮን ከፎክስ ውጪ ኦኤኤን እና ኒውስማክስ የተባሉ ወግ አጥባቂ ሚዲያዎች ላይም ክስ መሥርቷል።

ሌላ የድምጽ መስጫ ማሽን የሠራ ድርጅትም ፎክስ ስሜን አጥፍቷል ብሎ የ2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ክስ መሥርቷል። በተጨማሪም የትራምፕ ደጋፊዎች ሩዲ ጁልያኒ፣ ሲድኒ ፖዌል እና ማይክ ሊንደልን ከሷል።



# ስፖርት

## የሞተር ስፖርት ውድድሮችን በቴክኖሎጂ ለማገዝ ጥረት እየተደረገ ነው

ዓለማየሁ ግዛው


በሞተር ስፖርት በዓለም ላይ ከስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሚንቀሳቀስ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ባደጉት ሀገራት ይህ ስፖርት ተወዳጅና ከፍተኛ ሽልማትን ከሚያስገኙ የስፖርት ውድድሮች ጎራ ይሰለፋል። በአፍሪካም ሴኔጋልን በመሳሰሉ ሀገራት ሰፊ እንቅስቃሴ የሚደረግበት ሲሆን ቢያንስ በዓመት አንዴ የሚካሄደው ደማቅ ውድድር በፌስቲቫል ደረጃ የሚከናወንና እንደ አንድ የቱሪስት መስሕብ የሚያገለግልም ነው።

ያም ሆኖ የስፖርቱ ባሕሪ ከተሽከርካሪ ጋር የተገናኘ እንደመሆኑ እጅግ ከባድና አሰቃቂ ለሆነ አደጋ የመጋለጥ እድሉ ሰፊ በመሆኑ ጥንቃቄንም ይሻል። ስፖርቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰባቸው ሀገራት በሚደረጉ ውድድሮች እጅግ ዘመናዊ መኪኖችና ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። የስፖርቱ መወዳደሪያ ስፍራም ደረጃውን የጠበቀና ሰፊ ዝግጅት ተደርጎበት የሰለጠነ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ ለውድድሮች ስኬት ትልቅ ድርሻ ይወጣሉ።

በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅና ዝነኛ ከሆኑት የዓለማችን የሞተርና የመኪና ውድድሮች መካከል ፎርሙላ ዋን (Formula one)፣ የሞናኮ ግራንድ ፕሪክስ፣ ዳካር ሪሌይንና ሪሌይ ፊንላንድ ይጠቀሳሉ። እነዚህን ውድድሮች ለማዘጋጀትም የሚጠይቀው በጀት እጅጉን ከፍተኛ ነው። በዚህ ደረጃ ተወዳጅና ከፍተና ወጪን የሚጠይቅ ድግስ ለማዘጋጀት የስፖርቱን ማደግ ብቻ ሳይሆን የሀገራትን ፈርጣማ የኢኮኖሚ ጡንቻን ይፈልጋል።

ኢትዮጵያ ቀደም ባሉት ዓመታት ከውጪ ሀገራት ጭምር በሚመጡ ተወዳዳሪዎች የሞተር ስፖርት ውድድሮች በየጊዜው ታስተናግድ ነበር። ስፖርቱ በኢትዮጵያ ተቀባይነትን ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ በሕግና ሥርዓት በአሶሴሽን እየተመራ ይገኛል።

ስፖርቱ በኢትዮጵያ በርካታ ዓመታትን ቢያስቆጥርም የዕድሜውን ያክል ማደግ ግን አልቻለም። በኢትዮጵያ በሚዘጋጁ ውድድሮች ወጪዎችን የሚሸፍኑት እራሳቸው ተወዳዳሪዎች መሆናቸው ውድድሮችን በስፋት እንዳይካሄዱ እንቅፋት ከሚሆኑ ምክንያቶች አንዱ ነው። በተጨማሪም ስለስፖርቱ ያለው ግንዛቤ



አሶሴሽኑ ዘመናዊ መሣሪያዎችን በሀገር ውስጥ ውድድሮች በስፋት ለመጠቀም ከዓለም አቀፉ የሞተር ስፖርት ፌዴሬሽን ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል፣

አናሳ መሆን ለስፖርቱ አለማደግ የራሱ ድርሻ አለው። እነዚህንና መሰል ችግሮችን በመቅረፍ በቀጣይ በስፖርቱ የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠርና አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ሞተር ስፖርት አሶሴሽን አስታውቋል።

አሶሴሽኑ ብዙ ችግሮች ቢኖርበትም የሚያዘጋጃቸውን ውድድሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ማገዝ እንደጀመረ ጠቁሟል። በተለይም ቴክኖሎጂዎቹ ተወዳዳሪዎች ውድድራቸውን በትክክል መጨረሳቸውን ለመከታተል እንደሚያግዙም ጠቅሷል። አሶሴሽኑ የሞተር ስፖርት ውድድሮች በሚካሄዱበት ወቅት አቅጣጫ ጠቋሚ (ጂፒ ኤስ) ቴክኖሎጂንና ሌሎች ዘመናዊ መሳሪያዎችን በመጠቀም ውድድሮችን መከታተል (ሞኒተር) ማድረግ መጀመሩን ገልጿል። ቴክኖሎጂዎቹን በቅርቡ በመጋቢት 17 በአዲስ አበባ ሞተር ስፖርት አዘጋጅነት በተካሄደው ወድድር ላይ መጠቀም የተቻለ ሲሆን፣ መሣሪያዎቹ በውድድሮች ማጭበርበርን በማስቀረት በዳኝነት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን እንደሚቀርፉም ጠቁሟል።

የአሶሴሽኑ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ መዘምር ሰይፈ፣ ስፖርቱ ዘመናዊና ከሳይንስ፣ ምሕንድስና እንዲሁም ሒሳብ ጋር ልዩ ቁርኝት ስላለው ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቁ አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ። ስፖርቱን በማሳደግና ተሳትፎውን በመጨመር ለሀገር ገጽታ ግንባታም መጠቀም እንዲቻል ከዘመኑ ጋር አብሮ መራመድ የግድ መሆኑን ያስረዳሉ።

በሞተር ስፖርት ውድድሮች መንገድ ላይ የሚካሄዱ ፉክክሮችን ትክክለኛ መመዘኛ በመጠቀም ተሽከርካሪን በፍጥነት አሽከርክሮ እራስንና ሌሎችን ከጉዳት በመጠበቅ ማጠናቀቅ መቻል ትልቁ ጉዳይ ነው። ለዚህም ተሽከርካሪን በጥንቃቄ መያዝና ከጉዳት መጠበቅ ያስፈልጋል። ለዚህም አሶሴሽኑ ስፖርቱን የሚጠቅሙና የሚሳድጉ ዘመናዊ መሣሪያዎችን በሀገር ውስጥ ውድድሮች በስፋት ለመጠቀም ከዓለም አቀፉ የሞተር ስፖርት ፌዴሬሽን ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል። በዚህ ዓመትም ከዓለም አቀፉ የሞተር ስፖርት ፌዴሬሽን ስምንት ጎ ካርት የተሰኙ ግምታዊ ዋጋቸው ከ1 ሚሊዮን 1መቶ ሺ በላይ የሆኑ የታዳጊዎች መወዳደሪያ በድጋፍ ማግኘቱን ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገልጸዋል። እነዚህ መወዳደሪያዎች እጅግ ዘመናዊና የአሶሴሽኑ ስምና ዓርማ የተደረገባቸው ሲሆኑ በስፖርቱ ለሚደረጉ ቀጣይ እንቅስቃሴዎች ጉልህ ሚናን እንደሚጫወቱም አስረድተዋል። ይህም የታዳጊዎች የጎ ካርት ሥልጠናዎችን ለመስጠት ይረዳል ተብሎ ይጠበቃል። በአሁኑ ወቅት ዕድሜያቸው ከ13- 17 የሆኑ 22 ታዳጊዎች ሥልጠናቸውን በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ በመከታተል ላይ እንደሚገኙም አስታውሰዋል።

አሶሴሽኑ በቀጣይ የተለያዩ ውድድሮችን ለማከናወን እቅዱን ለባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ማቅረቡን የጠቆሙት አቶ መዘምር፣ አንደኛው የከተማ ውስጥ ውድድር ሲሆን በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ውድድሮችን ለማድረግ አሶሴሽኑ እቅድ እንዳለው ተናግረዋል። ሁለተኛው ደግሞ ከከተማ ውጪ የሚደረግና የደጋ ራሊ የሚባለውን ውድድር ለማካሄድ ታቅዷል።

አሶሴሽኑ የዳኞችና የአሰልጣኞች ሥልጠና ለመስጠት ያቀደ ሲሆን፣ የመወዳደሪያና የማሰልጠኛ ማዕከል ችግር እንዳለበት ይታወቃል። ለጊዜው ግን ለሚያደርገው ሥልጠናና ልምምድ የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚን እንደሚጠቀም የተጠቆመ ሲሆን፤ በቀጣይ የራሱ የሥልጠናና መለማማጃ ማዕከል ለማግኘት ጥረት በማድረግ ላይም ይገኛል። አሶሴሽኑ ከዚህ በፊት ሳንሱሲ አካባቢ የውጪ ውድድሮች ጭምር የሚካሄዱበት ስፍራ ቢኖርም ለልማት በመፈለጉ ምትክ ቦታ ለማግኘት እየተጠባበቀ እንደሚገኝ አቶ መዘምር የገለፁ ሲሆን፣ በአጠቃላይ የሥልጠና፣ የመለማመጃንና የውድድር ቦታን ልዩ ባሕሪ መረዳት አለመቻል ብዙ ችግር እንደሆነም አክለዋል።

የተወሰኑ አመራሮች ለስፖርቱ የሚሰጡት ግምትና ጥሩ ያልሆነ ግንዛቤ ስፖርቱን እንዳያድግ እንቅፋት እንደፈጠረ የሚናገሩት አቶ መዘምር፣ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን በክልሎችም በማስፋት እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

አሶሴሽኑ በቀጣይ እነዚህንና መሰል ችግሮችን በመቅረፍ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በአሕጉራዊና ዓለም አቀፍ ውድድሮች የመሳተፍ ዓላማን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ በቀጣይ ግንቦት ወር ለሚደረገው የከተማ ውስጥ የመኪና ውድድር ዝግጅት መጀመሩ ታውቋል።


## የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 04/2015 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ባህ/ዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ለወረታና ጎንደር ጉምሩክ የሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ማለትም ለወረታ ጉምሩክ ጠዋት ቢሮ መድረሻ 1:55 ፣ ምሳ ስአት ከቢሮ ወደ ቤት መነሻ ሰዓት 6:05፣ ከቤት ወደ ቢሮ መመለሻ ሰዓት 6፡55፣ ከቢሮ ወደ ቤት መመለሻ መነሻ አት11፡05 ሲሆን ለጎንደር ለማመላለስ በግልጽ ጉምሩክ ጠዋት ቢሮ መድረሻ 1፡55 እና ማታ ከቢሮ ወደ ቤት መመለሻ መነሻ ሰዓት 11:05 ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል በመሆኑም በጨረታዉ መሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች /አቅራቢዎች/ ከዚህ በታች የተጠየቁትን መስፈርቶችና ግዴታዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

1. በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ የቲን ሰርተፍኬት ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ስለመሆናቸዉ ማስረጃ (ክሊራንስ) ማቅረብ የሚችሉ፣ የባለቤትነት ማስረጃ ወይም ሊብሬ ፣የኦፕሬተርነት ፈቃድ ፣አመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት ቦሎ/ያደረገ፣
2. በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ማለትም የንግድ ስራ ፈቃዳቸው የየብስና ተዛማጅ አገልግሎት ሆኖ ሊብሬው ለንግድ የሚል ወይም የንግድ ስራ ፈቃዳቸው አገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሆኖ ሊብሬው የመኪና ማከራየት የሚል፣
3. የጨረታ ማስከበሪያ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በመስመር 10,000/አስር ሽህ/ በባንክ በተመሰከረለት ቼክ (C.P.O) ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዞ ማቅረብ የሚችሉ፤
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን 100 /መቶ ብር / ብቻ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 15 ቀናት ውስጥ በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር በአፄ ቴወድሮስ ክ/ከተማ ወደ ዲያስፖራ በሚወስደው አስፓልት መንገደ የአማራ ህንጻ ስራዎች ኮንስትራክሽ ድርጅት ጎን በሚገኘው የጉምሩክ ኮሚሽን ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 304 በመቅረብ የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፤
5. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ሰነድ በጥንቃቄ በመሙላት በሚገባ በኢንቨሎፕ /ፖስታ/ በማሸግ እና ዋጋ መሙያው ላይ የድርጅቱን ማህተምና ፊርማ በግልጽ በማስቀመጥ ለዚህ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
6. የጨረታ ሳጥኑ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ16ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመስሪያ ቤቱ 3ኛ ፎቅ የግዥ ክፍል ቢሮ ቁጥር 306 ጠዋት 4:30 ይከፈታል ነገር ግን 16 ኛው ቀን የህዝብ በዓል/እሁድ/ ከሆነ በ17ኛዉ ቀን 4:00 ሰአት ተዘግቶ 4:30 ሰዓት ይከፈታል።
7. የጨረታ አሸናፊው የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና የዓመቱን ጠቅላላ ዋጋ 10% አስር በመቶ) በጥሬ ገንዘብ ወይንም በባንክ በተመሰከረለት ቼክ (C.P.O) ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራት በማስያዝ ከመ/ቤቱ ጋር ውል መፈራረም ይኖርባቸዋል::
8. ተጫራቾች ዝርዝር ሁኔታ /መግለጫ/ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ያገኙታል፣
9. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
10. ተጫራቾች ከላይ የተጠቀሱትን የንግድ ማስረጃዎች ኦርጅናል ለብቻው አቅርበዉ ማሳየት ይኖርባቸዋል::

**ለበለጠ መረጃ:- በስልክ ቁጥር 0583207051/0583206641/0582263346/**

**በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ባህ/ዳር ቅ/ጽ/ቤት**

## ሐረሪ ክልል

መሀመድ አደም ስም ተመዝግቦ ስለሚገኝ የሰሌዳ ቁጥር 01-05817 ሐረ የሆነ ተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ በማንኛውም መልኩ ይዤዋለሁ የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ባያመለክቱ ምትክ ሊበሬ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን።

**የሐረሪ ሕ/ክ/መንግሥት የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ጽ/ቤት**

## ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

በከሳሽ ደቡብ ክልል ፍትህ ቢሮ እና በተከሳሾች 1ኛ. አብድላጥፍ ሰልማን፣ 2ኛ.ራመቶ ከድር 3ኛ. በርገና አብዶ 4ኛ.ሰመረ ሪቦ 5ኛ አወል ሪባዮ 6ኛ. በርገና ሸ/አደም 7ኛ መሀመድ ኡመር 8ኛ. ከይሩ ኡስማን 9ኛ አጥያ ከድር 10ኛ.ሱራጅ ጥቃሞ መካከል ስላለው ከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ ጉዳይ ተከሳሾች ያለ በቂ ምክንያት ክሱ በሚሰማበት ወቅት ፍ/ቤት ሊቀርቡ አልቻሉም::

በመሆኑም ተከሳሾች በዚህ ማስታወቂያ በተገለጸው መሰረት የፍ/ቤቱን ቀጠሮ አውቀው ለሚያዝያ 25/2015 ዓ/ም ለሆነው ቀጠሮ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ ያሰውቃል።

**ሀላባ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

## በአዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-2278 የተሽከርካሪው አይነት ሞተር ብስክሌት የሻንሲ ቁጥር DG01X-040658 ሞዴል DT175 የሞተር ቁጥር 3T1S-121627 የሊብሬ ቁጥር 251803 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/7/2015 አመልክተዋል።

ሠሌዳው ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**